ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 349 ነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ወንጀለኞችን የሚገራ ሕግ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

**ዜና ትንታኔ**

ዕርስ በዕርስ ተዋዶ፣ ዘመድ ባዕድ ሳይል አንዱ ለሌላው መከታ ሆኖ በኖረባት ሀገራችን ጠባቂ የተባለው አጥቂ፣ ከጉዳት ሊታደግ የተገባው ሕይወት ነጣቂ ሲሆን እየሰማን ነው። ማኅበረሰብ ላይ ዘላቂ ሥነ ልቡናዊ ጫናና ቁስል ጥለው የሚያልፉ ወንጀሎች እየተበራከቱ መጥተዋል። በተለይም በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ቁጥራቸውና አሰቃቂነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።

ከሰሞኑም ከአንድ ዓመት በፊት የተፈጸመና የሕዝብን ልብ የሰበረ አሰቃቂ ወንጀል በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ተሰምቷል። በ7 ዓመቷ ሕጻን ሔቨን አወት ላይ የተፈጸመን ዘግናኝ ወንጀል አስመልክቶ አስተያየት የሚሰጡ ወገኖች በወንጀል ፈጻሚዎች ላይ ጠንካራና ለሌላው መማሪያ የሆነ ርምጃ አለመወሰዱ እንዲህ ላሉ ወንጀሎች መበራከት ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎቻችን፣ ከሰው ተፈጥሯዊ ባሕርይ ያፈነገጡ ወንጀሎች እምብዛም በማይሰሙበት ጊዜ የወጡ መሆናቸውና፣ የአሁን ዘመን አረመኔያዊ ወንጀሎችን የሚገሩ ሆነው አለመሻሻላቸው፣ ወንጀለኞች ለፈጸሙት ወንጀል ተመጣጣኝ የሆነ የፍርድ ውሳኔ እንዳይሰጣቸው ምክንያት ሆኗል የሚለውም ሀሳብ ከሕዝብ ዘንድ አመዝኖ ይደመጣል።

ለመሆኑ በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መበራከት ምክንያቱ ምን ይሆን? በ7 ዓመቷ

ወንጀለኞችን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል










## ዲያስፖራው በሀገሩ ልማት ያለው ተሳትፎ

መዓዛ ማሞ

**ዜና ትንታኔ**

በተለያየ መንገድ ከሃገራቸው የወጡ ዲያስፖራዎች ተመልሰው ሃገራቸውን በገንዘብ፣ በእውቀት እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ማገዝ የተለመደ ነው። ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎችም መጠኑ ይለያይ እንጂ በተለያየ መልኩ ለሃገራቸው ድጋፍ ያደርጋሉ።

የታላቁ የህዳሴ ግድብ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ 2016 በጀት ዓመት መጨረሻ አንድ ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ በቦንድ ግዢ እና በስጦታ ከዲያስፖራው መገኘቱ ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት

ዲያስፖው ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል








## አረንጓዴ - የሠላም ዐሻራዎች

አዲሱ ገረመው

**ዜና ትንታኔ**

ኢ-ተገማች በሆነ ሁኔታ የክረምት ፀሐይ ወርቃማ ቀለሟን በተራራው ላይ ስትጥል፣ ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት ችግኝ ለመትከል ከያሉበት እየጐረፉ ነው። በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ ዓይንን በሚስቡ ኮረብታዎች ውስጥ የማኅበረሰብ የልማትና የሠላም መንፈስ በመልከዓ ምድሩ ውስጥ ይንሰራፋል።

እዚህ፣ በአረንጓዴ ሸለቆዎች እና ተራሮች መካከል፣ ችግርን የመቋቋም፣ የተስፋ እና የቁርጠኝነት ታሪክ ይገለጣል። የወረባቦ ሕዝብ ከፀጥታ ጋር ተያይዞ የሚፈጥሩ ችግሮችን በራሱ በመፍታት ሠላም ቀጣና ውስጥ ይገኛል። ለዚህም ነው የአካባቢው ማኅበረሰብ የአንድ ጀምበር የ600 ሚሊዮን የችግኝ ተከላ መርሐ ግብርን በስፋት የተሳተፈው።

ክልሉ ከገባበት የፀጥታ ችግር አኳያ ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተሳትፎና የተቀናጀ የልማት ተነሳሽነት የኅብረተሰቡን የሠላምና የልማት ፍላጎት ማሳያ ሆኗል። የወረባቦ ወረዳ ቀበሌ 01 ነዋሪ ወይዘሮ አሚና ሰይድ የዚህን የጋራ ጥረት ፋይዳ ሲያንጸባርቁ፣ "እዚህ ያሉት ሰዎች የሠላም ወዳጆች ናቸው። እኛ ለልማት ቆመናል። ሠላምን የሚያደፈርሱ ጉዳዮች አሉ። ነገር ግን ችግኞችን ያለችግር እየተከልን

አረንጓዴ-... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ዜና



አቶ ጥላሁን ከበደ

# ክልሉ በተፈጥሮ አደጋ የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን እያከናወነ ነው

- ከ 3 ሺህ በላይ አባወራዎችን በቋሚነት ለማስፈር ዝግጅት እየተደረገ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በመሬት ናዳና በጎርፍ አደጋ ምክንያት የተፈናቀሉ 19ሺ 847 ዜጎችን የመደገፍ እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ የክልሉ መንግሥት ገለጸ።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በዚህ ክረምት ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች የደረሱ የመሬት ናዳዎች እና የጎርፍ አደጋዎች በርካታ ሰዎችን ለሞት እና ለመፈናቀል ዳርገዋል። ክልሉ በአሁኑ ጊዜም የተፈናቀሉ ዜጎችን የመደገፍ እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን እያከናወነ ነው።

በክረምቱ ወቅት በዝናብ መጠን መጨመር ምክንያት በክልሉ ያጋጠሙ አደጋዎች እጅግ አሳዛኝ እንደነበሩ አስታውሰው፤ በጎፋ ዞን በአጋጠመው የመሬት መደርመስ አደጋ ለ249 ዜጎች ሞት፣ በወላይታ ዞን ለ12 ዜጎች ሞት፣ በጋሞ ዞን ለ5 ዜጎች ሞት እንዲሁም በባስኬቶ ንብረት ውድመት ያደረሰ መሆኑን ተናግረዋል። በጎርፍ ምክንያትም ደቡብ አሞ ዳሰነች ወረዳ ላይ መፈናቀል ማጋጠሙንም ተናግረዋል።

እንደ ጊዜያዊ መፍትሔ ለናዳ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ጋርዱላ ዞኖችን በማጥናት ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ወደ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች እንዲወጡ መደረጉንና በቋሚነት ተጠንቶ በሰፈራ መልክ ለማቋቋም ሥራ መጀመሩን አብራርተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 19ሺህ 847 ተፈናቃዮች በጊዜያዊ መጠለያዎች እንደሚገኙ የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ክልሉ የተፈናቀሉ ዜጎችን የመደገፍ እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

የተፈናቀሉትን ሁሉ በቋሚነት ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር አስቸጋሪ መሆኑን ተናግረው፤ የሰው ልጅ ቢኖርባቸው አስጊ የሆኑትንና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቢሠራባቸው መኖር የሚያስችሉ ቦታዎችን የመለየት ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

ሰዎች በቀጣይነት ቢኖሩበት አደገኛ በሆኑ ቦታዎች የነበሩ ዜጎችን ወደ ሌሎች ስጋት ወደ ሌለባቸው ቦታዎች በስግሰጋ እና በሰፈራ በቋሚነት እንዲሰፍሩ እንደሚደረግ የተናገሩት አቶ ጥላሁን፤ በዚህም በመጀመሪያ ዙር 627 አባወራዎች እንዲሰፍሩ የሚደረግ ሲሆን በሁለተኛ ዙር ደግሞ 2ሺህ 394 አባወራዎች ሰፈራ እንደሚደረግ ጠቁመዋል። ሰፈራውን ለማከናወንም ክልሉ ዝግጅቶች እያደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሌሎች በጥናት የሚለዩ መሆናቸውን ገልጸው፤ ለመኖር በሚያስችሉ ቦታዎች ላይ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራዎች ተሠርተው በቦታቸው የሚመለሱ ተፈናቃዮች እንደሚኖሩ አመላክተዋል።

# በተሽከርካሪ ለሚደርስ ሞትና የአካል ጉዳት የሚፈጸመው የሦስተኛ ወገን መድን ክፍያ ተሻሻለ

**ዘሳስም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- በተሽከርካሪ አደጋ ለሞት እና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ለአስቸኳይ ሕክምና ይከፈል የነበረውን የገንዘብ መጠን ያሻሻለ ደንብ ተግባራዊ መሆኑን የመንገድ ደኅንነት እና መንገድ ፈንድ ገለጸ።

በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የሚከፈለውን የአረቦን ተመን የካሳ መጠን ክፍያ ለመወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 554/2016 ተግባር ላይ ውሏል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አባሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ደንቡ በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ለአስቸኳይ ሕክምና ሁለት ሺህ ብር ይከፈል የነበረውን ወደ15 ሺህ ብር አሳድጓል።

በተሽከርካሪ ጉዳት ለሞት ይከፈል የነበረው ካሳ 40 ሺ ብር እንደነበር በማስታወስም፤ ለሞት የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን ወደ 250 ሺህ ብር ማደጉንም ነው የገለጹት።

ውሳኔው የብር ግሽበትና ሌሎች ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተሻሻለ መሆኑን ተናግረዋል። የተሽከርካሪ አደጋ ለደረሰበት ሰው ሕክምና ይመደብ የነበረው ሁለት ሺህ ብር አነስተኛ ነው በሚል ሰፊ ቅሬታ ሲነሳበት የቆየ መሆኑን አመልክተዋል።


የተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ማንኛውም ሰው በየትኛውም ሆስፒታል በሀገር አቀፍ ደረጃ የነፃ ሕክምና አገልግሎት እንደሚያገኝም ነው የገለጹት።

ይህንን ገንዘብ ለመሸፈን ኢንሹራንስ ፕሪሚየም፣ ማለትም የሦስተኛ ወገን የኃላፊነት ክፍያዎች ላይም ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ የሚከፍሉት ግብር ጭማሪ እንዲደረግ ውሳኔ መተላለፉን ተናግረዋል።

በአዲሱ የሦስተኛ ወገን የኃላፊነት መመሪያ መሠረት ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት በፊት ተቀምጦ የነበረው ሁለት ሺህ ብር ወደ 15 ሺህ ብር ከፍ ማለቱን ተከትሎ በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የሚከፈለው የአረቦን ተመን የካሳ መጠን ላይ መጠነኛ ጭማሪ ተደርጓል ነው ያሉት።

በተሽከርካሪዎች ላይ የሦስተኛ ወገን ተለጣፊ አስገዳጅ ሕግ፣ በየዓመቱ ይከፈል በነበረው ላይ ጭማሪ ተደርጎ እንደሚከፈልም ጠቁመዋል።

እንደሲሲያቸው መጠን ተሽከርካሪዎች የሚከፍሉት ገንዘብ የሚለያይ ሆኖ፤ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ብር አካባቢ፤ ከባድ ተሽከርካሪዎች ደግሞ እስከ 11 ሺህ ብር ገደማ የሚደርስ ፕሪሚየም የዓመት ክፍያ ሽፋን እንደሚኖርባቸውም አመልክተዋል።



# የኢትዮጵያ ተጨማሪ የዲፕሎማሲ ክንድ - አረንጓዴ ዐሻራ

**ሄለን ወንድምነው**

**ዜና ሐተታ**

አረንጓዴ ዐሻራ በኢትዮጵያ መተግበር ከጀመረ ስድስት ዓመታት ሆኖታል። በስድስት ዓመታት ጉዞውም 40 ቢሊዮን የሚጠጉ ችግኞች ተተክለዋል። ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ የሀገሪቱን የደን ሽፋን በስድስት በመቶ መጨመር ተችሏል።

አረንጓዴ ዐሻራ ለምለሚቷን ኢትዮጵያ ዕውን ያደርጋል። የምግብ ዋስትናን ያረጋግጣል። ለከተማ ውበት፣ ለቱሪዝምና ለኢንዱስትሪ ዕድገትም አይተኬ ሚና አለው። የሥነምሕዳር መናጋትንም ያክማል። ዓለምን እያናወጣት ላለው የአየር ብክለትም ፈውስ ነው። ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ስሟን እያስጠራና ተደማጭ እያደረጋት ነው።

የአረንጓዴ ዐሻራ በርከት አያሌ መሆኑን ኢትዮጵያውያን ከተገነዘቡ ሰነባብተዋል። ጠቀሜታ ከኢትዮጵያ ያልፋል። ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ያለፈውን የአረንጓዴ ዐሻራ በረከት ለዓለም ሀገራት ለማቋደስ በተባበረ ክንዳቸው ተነስተዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ አደፍርስ ወርቁ (ዶ/ር) ስለአረንጓዴ ዐሻራ ይናገራሉ። መርሐግብሩ ኢትዮጵያውያንን ከተፈጥሮ ጋር እያስታረቀ ነው። ለሀገሪቱ የዲፕሎማሲ እድገትም ድርሻ አለው። አረንጓዴ ዐሻራ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አስከብሯል። ከጎረቤቶቿም መልካም መስተጋብርን ፈጥሮላታል።

አደፍርስ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ በተከለቻቸው ችግኞች ማስቀረት የቻለችውን የደን ጭፍጨፋ እና ያለማችውን ሥነምሕዳር በዓለም መድረኮች እያቀረበች ነው ይላሉ። በዚህም ሌሎች ሀገራት ተሞክሮዋን በማካፈል በርካታ ሀገራት ለአረንጓዴ ዐሻራ እየተነሳሱ ነው።

በኢትዮጵያ የሚተከሉ ችግኞች ለጎረቤት ሀገራትና ለሌሎች አካባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በዚህ ደግሞ ማንም ስለኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር ሲናገር ይደመጣል ሲሉ ይናገራሉ።

ከሁለት ዓመት በፊት የኬኒያ መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ከኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር አተገባበር ልምድ መውሰድ እፈልጋለሁ ብሎ መጠየቁን የሚያስታውሱት አደፍርስ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያም ያላትን ተሞክሮ አካፍላለች። ኬኒያም ችግኞችን በቢሊዮን አቅዶ መትከል እንደሚቻል ተምራለች። ኬኒያ ከኢትዮጵያ ቀጥሎ ችግኞችን በቢሊዮን ያቀደች ሀገር ሆናለች። ይህም ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ሚና አለው ይላሉ።

ሌላኛው የኢትዮጵያ ተፅዕኖ መካከለኛው ምሥራቅ ላይ ነው። በሳዑዲ መንግሥት የሚመራውን የመካከለኛው ምሥራቅ የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ካውንስል ሲያቋቁም የኢትዮጵያ መንግሥት አባል እንዲሆን ተጠይቋል። ኢትዮጵያ ችግኝ በመትከል፣ በመንከባከብና ልምላሜን በመጨመር የሠራችውን ሥራ እንድታካፍል ተጠይቃለች ይላሉ። ይህም ለኢትዮጵያ አንድ ተጨማሪ ወንበር የማዘጋጀት ያህል ነው ይላሉ።

በኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የልቀት ቅነሳ መርሐግብር መዘጋጀቱን በመግለጽ፤ በ68 በመቶ ልቀትን ለመቀለስ ታቅዶ እየተሠራ ነው። በዚህም ዲፕሎማሲን ማሳደግ ይቻላል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ለኢትዮጵያ ተጨማሪ የዲፕሎማሲ ክንድ እየሆነ ነው ይላሉ።

የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ ትሩፋት ከሀገር ያለፈ ነውና ማንም ሲናገር አበጀሽ ኢትዮጵያ እያስባላት ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ አጠቃላይ ካላት 112 ሚሊዮን ሄክታር ስፋት ውስጥ 54 ሚሊዮን ሄክተሩ የተለያየ ዓይነት የሥነምሕዳር መናጋት የሚታይበት መሆኑ በጥናት የተረጋገጠ መሆኑን ይናገራሉ።

ይህንን የሥነምሕዳር መናጋት ለማከም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር እየተተገበረ ነው። በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬትን በችግኝ ለመሸፈን መታቀዱን ያስረዳሉ።

አንድ ሚሊዮን ሄክታሩ ላይ ችግኞችን መከታተል እንዲያስችል ጂኦሪፈረንስ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የተጀመረው የሥነምሕዳር መናጋትን ለማከም፣ ምርትና ምርታማነትን እና የደን ሽፋንን ለማሳደግ መሆኑን ይገልጻሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከስሜታዊነት በመራቅ ስፖርቱን መታደግ የግድ ነው!

ኢትዮጵያን በዓለም ዙሪያ በበጎ እንድትታወቅ ያደረጋት እና በስፖርቱ የዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ተሳትፏችን በሚመዘገቡ ውጤቶች ከፍተኛውን ደስታና ኩራት እንድናጣጥም የሚያደርገን የአትሌቲክስ ስፖርት ነው። ይህ ልዩ መታወቂያችን የሆነ ስፖርት ከቅርብ ግዜ ወዲህ በገጠመው አስተዳደራዊ ብቃት ማነስ ችግር ሲንገላታ እየታየ ይገኛል።

በፓሪሱ ኦሊምፒክ የሚጠበቀውና የተለመደው የሜዳሊያ ቁጥር አለመገኘት ስፖርቱ በተሳሳተ ሐዲድ ላይ እየተጓዘ መሆኑን በግልፅ ያሳየ በመሆኑ ትኩረቱን የበለጠ አድርጎት ይሆናል። እርግጥ መለኪያው ውጤት እና ሜዳሊያ ነው። ይሁንና ከዚያ ጀርባ ለውጤቱ መውደቅ የመጣንበትን መንገድ መርሳት ግን ተገቢ አይሆንም። በአደረጃጀት እና ኃላፊነት ግን የታዩትን ችግሮች እንዴት እና ለምን የሚለውን ለይቶ ማየት ተገቢ ነው።

አንዱ ሌላው ላይ በመግለጫ ጋጋታና በማኅበራዊ ሚዲያው ከሚያደርገው ድንጋይ መወራወር መቆጠብ ያስፈልጋል። ስፖርቱ ከገባበት አዘቅት የሚወጣበትን መፍትሔ መፈለግ ብቻ ነው አዋጩ መንገድ። አሁን እየሄድንበት ያለው መንገድ የስፖርቱን የቁልቁለት ጉዞ ያፋጥነዋል እንጂ የከፍታ ስኬትን ማምጣት አይቻለውም። የሚያበሳጩና ስሜትን የሚጎዱ ነገሮች ስለሌሉ ሳይሆን ስህተት በሌላ ስህተት መታረም ስለሌለበት ለእያንዳንዱ ጉዳይ ከዚህ በኋላ ምን ይደረግ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ቀጥሎስ ምን ይደረግ? ማለትም ያስፈልጋል። ከስሜታዊነት በወጣ መልኩ በስክነት መራመድ ተገቢ የሚሆነውም ለዚህ ነው።

ስፖርቱ አሁን ካለበት የአስተዳደር ችግር ወጥቶ በተሻለ ሁኔታ የሚመራበት ግዜ አሁን ነው። ስፖርቱ የሰው ብቻ ሳይሆን የአሠራር ለውጥ ያስፈልገዋል፤ ተጠያቂነት ሰፍኖ በሥርዓት የሚመራ ተቋም ለመገንባት ጊዜው አሁን ነው።

የስፖርት አመራሮች ከማንኛውም አላስፈላጊ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ትኩረታቸውን ስፖርቱን በማስፋፋቱ እና ማሳደጉ ላይ አድርገው የሚሠሩ ስለስፖርቱም በቂ እውቀት እና ፍቅሩ ያላቸው ቢሆኑ መልካም ነው። ለቦታው በሚመጥን እና ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት በሚችል የስፖርት አመራር የሚመራ የስፖርት ተቋምን መገንባት በተመሳሳይ ሰዓት የሀገር ግንባታን የሚደግፉ ሦስት ነገሮችን ስኬታማ ያደርጋል። በስፖርት ጤናውን የሚጠብቅ ማኅበረሰብ በመፍጠር በጤናው ሴክተር ላይ የሚኖረውን ጫና ይቀንሳል፣ በሀገር ገፅታ ግንባታ እና በኢኮኖሚው ዕድገት ላይም የበኩሉን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል።

አሁን የሀገራችንን የኦሊምፒክ ኮሚቴ እና የአትሌቲክስ ፌዴሬሽንን የሚመሩትን ሰዎች የሚመርጠው ጠቅላላ ጉባኤ ስብጥር እንዳለመታደል ሆኖ በዚህ ዓይነት የተዋቀረ አለመሆኑ ገሐድ ወጥቷል። በመሆኑም ተቋሞቹን ለመምራት የሚመረጡትን ሰዎች የሚሰይመው ጠቅላላ ጉባኤ በግዴለሾች የተሞላ እና በተሳሳተ መንገድ በሚጓዙ ግዜም ተጠያቂ የሚያደርጋቸው እንዳልሆነ ተደጋግሞ ታይቷል።

በቶኪዮ ኦሊምፒክ በትልቅ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረክ የሀገርን ክብር ዝቅ የሚያደርግ ጥፋት አጥፍተውም ደግሞ የሚመርጠው እነሱኑ መሆኑን ታዝበናል። በፓሪስ ኦሊምፒክ የዝግጅት ግዜ እንዲሁም በውድድሩ ወቅት የነበሩት አስተዳደራዊ ድክመቶች ተገምግመው በኦሊምፒክም ሆነ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ተጠያቂ የሚሆን አካል የሚኖርበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል።

በኦሊምፒኩ ኢትዮጵያ በዋነኝነት የምትጠራበት አትሌቲክስ ነው። በአትሌቲክስ ጉዳዮች ደግሞ ለምስጋናውም ለተወቃሽነቱም ዋናው ተቋም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው። ኦሊምፒክ ኮሚቴ ላይ የሚነሱት ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም የራሱን ኃላፊነት እና ድርሻ መውሰድ አለበት። አጠቃላይ አደረጃጀቱ ራሱን የቻለ ፍተሻ የሚፈልግ ተቋምም ነው። መርሕ እውነታ እና ሀገር ከሆነ ዓላማው ሁሉንም ከሁሉም አቅጣጫ አንፃር መቃኘት አስፈላጊ ነው።

ሕዝቡ ቅሬታውን በስፋት አሰምቷል፤ ስፖርተኞችና አሠልጣኞች ቅሬታቸውን ተናግረዋል፤ ባለሙያዎች ችግሩንና መፍትሔውን እየጠቆሙ ይገኛሉ። አብዛኛው ሚዲያም ለለውጥ ታግሏል፤ ይህ መቀጠል አለበት። አሁን የዱላ ቅብብሎሹ መንግሥት ጋር ደርሷል፤ መንግሥት ስፖርቱ ላይ ጣልቃ አይገባም የሚለው ሽፋን በብልሃት ሊታይ ይገባል። የሀገሪቱ ሕግ ተጥሶ አይቶ እንዳላየ በዝምታ ከመቀጠል ይልቅ የመፍትሔ አካል ሆኖ ለውጥ እንዲመጣ ማገዝ ግድ ይላል።

የኦሊምፒክ ኮሚቴ እንደማንኛውም የስፖርት ተቋማት መንግሥታዊ ተቋም አይደለም። ለትርፍም የተቋቋመ ድርጅትም አይደለም። ይህ ማለት መንግሥት መሰል ተቋማትን በቀጥታ አያስተዳድራቸውም፣ በሁሉም እንቅስቃሴያቸው በቀጥታ አይገባም ማለት ነው። ነገር ግን በሁሉም ጉዳይ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ማለት ደግሞ አይደለም።

መንግሥት ለዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ምን ምን እየተደረገ እንዳለ እና ያሉት ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ? የሚለውን እንዲታይለት የመጠየቅ የማስታወስ መብት አለው። እናም ይገባልም ይጠይቃልም ሲባል እንዴት? የሚለውን "አይ አይችልም" ሲባልም የት እና ምን ቦታ የሚለውን ለይቶ ማየት ከሁኔታዎች ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል። የአካሄድ ቅደም ተከተሎች መዛባት ውስጥ መግባትም ራሱን የቻለ ችግር እንዳይሆን ግን ከስሜታዊነት መራቅ የግድ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ቀጣና ማራቅ የሚቻል አይደለም

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር፤ የቀጣናው ወሣኝ ሀገር ናት። ወሣኝ መሆኗ ደግሞ ለራሷ ብቻ ሣይሆን በዓለም ፖለቲካ ቁልፍ ሚና ያላቸው ሀገራት የሚገነዘቡት ነው። ለምዕራባውያን ሆነ ለዓረቡ ዓለም በመልክዓ ምድር አቀማመጧ፣ ባላት የተፈጥሮ ሃብት ብሎም በዓለም ስትራቴጂክ እይታዎች አኳያ ቁልፍ ቦታ ላይ የምትገኝ፤ የችግር ቀን ፈውስ ናት።

የዲፕሎማሲ እና የዓለም የፖለቲካ ቢሆኖችን በአግባቡ የሚረዱ አካላት የኢትዮጵያን ሚና አግዝፈው ይመለከታሉ። ይህም በመሆኑ ይህችን ሀገር ሳይዙ በቀጣናው ላይ ወታደራዊም ሆነ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን መሞከር ትርፉ ልፋት ብቻ እንደሚሆን ብዙዎች ይስማማሉ።

አካባቢው ከሕንድ ውቅያኖስ እና ከቀይ ባሕር ጋር የሚገናኝ ነው፤ በተለይም ቀይ ባሕር የአፍሪካ፣ የአውሮፓ እና የኤዥያ አሕጉራትን የሚያገናኝ ትልቅ የንግድ አካባቢ ነው። የፈረጠመ አቅም ማሳያ ትልቁ ቀጣናም ነው። በመሆኑም በዚህ ቀጣና ሀገራት ኢትዮጵያን የሚጠጉት ሆነ የሚወዳጁት ለብሔራዊ ጥቅማቸው ነው።

በአሁኑ ወቅት ዓረቡ ዓለም ኢትዮጵያን ከምንጊዜም በላይ የሚፈልግበት ወቅት ላይ ነው። በነዳጅ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆኖ መቀጠል እንደማይቻል የተረዱት ይመስላል። ይህንን ተከትሎም የዓረቡ ዓለም ባለ ታላላቅ ኢኮኖሚ ባለቤት ሀገራት ለየት ያለ የኢኮኖሚ እይታ እየያዙ ነው።

በርካታ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትም በባሕል ውርርስም ሆነ በመልክዓ ምድራዊ ቅርርቦሽ ለእነዚህ ሀገራት ቅርብ መሆናቸው ስትራቴጂክ ተጠቃሚ የመሆን ዕድላቸውን አስፍቶታል። አሁን ላይ ያለው ጥያቄ ግን ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ይህን መልከ ብዙ እና ሰፋ ያለ ፍላጎት ማን ያሟላል የሚለው ነው። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ እና ተመራጭ ሀገር ናት።

በኢትዮጵያ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ 12 ወንዞችን ከለምለም አፈር ጋር ማገናኘት ይፈልጋሉ። ይህ የሚጠይቀው ቴክኖሎጂ ደግሞ ዓረቦቹ ካላቸው አሁናዊ ካፒታል አኳያ ‹‹ኢምንት›› ነው። ይህ ለዓረቡ ዓለም እፎይታን የሚሰጣቸው፤ ኢትዮጵያን ስትራቴጂክ አጋር አድርጎ ለመቀጠልም የሚያነሳሳቸው ነው።

ሀገራችን በተፈጥሮ ሃብት አቅም እንዳላት፤ በርካታ ምሑራን የሚስማሙበት እና ዓለም የሚያውቀው ሐቅ አለ። ኢትዮጵያ ያላት የተፈጥሮ ሃብት፣ መልክዓ ምድር ስፋትና የሕዝብ ብዛት ሀገራት ትኩረታቸውን እንዲጥሉባት አድርጓል። የሀገሪቱ አየር ፀባይና የአየር ንብረት ባሕሪ በሌሎቹ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ሕዝብም ትልቅ ሃብት ነው፤ በተለይ ደግሞ በነፃነት የኖረ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ወሳኝ ስለመሆኑም ምሑራን ይናገራሉ።

> **ሀገራችን በተፈጥሮ ሃብት አቅም እንዳላት፤ በርካታ ምሑራን የሚስማሙበት እና ዓለም የሚያወቀው ሐቅ አለ፡፡ ኢትዮጵያ ያላት የተፈጥሮ ሃብት፣ መልክዓ ምድር ስፋትና የሕዝብ ብዛት ሀገራት ትኩረታቸውን እንዲጥሉባት አድርጓል**

ኢትዮጵያ ከማሕፀኗ የሚወጡ 12 ወንዞችን ወደ ጎረቤት ሀገራት ይፈሳሉ። ሸበሌ ወንዝ ወደ ሶማሊያ፣ ኦሞ ወንዝ ወደ ኬኒያ፣ ገናሌ ወንዝ ወደ ኬኒያ እና ሶማሊያ፣ ዓባይ ወንዝ ደግሞ በርካታ ሀገራትን እየነካካ የሚያልፍ ነው። እነዚህን የተፈጥሮ ትሩፋቶች በቅርብ ርቀት የሚመለከቱት የዓረቡ ዓለም ሀገራት የትሩፋቱ ተካፋይ ለመሆን ያላቸው የኢኮኖሚ አቅም ይፈቅድላቸዋል።

ሌላኛው ጉዳይ በዓለም ላይ ስጋት እየሆነ የመጣው የሽብርተኝነት ስጋት ምዕራባውያን በቀጣናው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል። ስጋታቸውን ለማርገብ በቅድሚያ ስትራቴጂክ አጋር አድርገው የወሰዱት ኢትዮጵያ ነው። ከዚህ አኳያ በሶማሊያ የአሸባሪን አልሸባብ ሴል ለመበጣጠስ በቀዳሚነት ኃላፊነቱን የወሰደው እና ትልቅ ውጤት ያስመዘገበው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነው።

በዚህ ረገድ ደግሞ ሰፋ ባለ ሁኔታ የቀይ ባሕር ቀጣና ሠላማዊ ሆኖ እንዲዘልቅ ኢትዮጵያን የመሰሉ ጠንካራ የሠራዊት አደረጃጀት ያላቸው ሀገራት በአሜሪካውያን እና በምዕራባውያን ተመራጭ ናቸው። ሀገራቱ ብሔራዊ ጥቅማቸውን በማስከበር ሂደትም የኢትዮጵያ ሚና ወሳኝ ነው።

እነዚህ የተፈጥሮ ፀጋዎችና ስትራቴጂክ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ቀጣና አይተኬ ሚና እንዳላት ቢያመለክትም፤ ይህን እውነታ በአንድም ይሁን በሌላ በራሳቸው ይሁን በሌሎች ተፅዕኖ መቀበል የማይፈልጉ ሀገራት መኖራቸውን ማወቅ ተገቢ እና እንደ ሀገር አሁን ላይ የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች ለመሻገር ግድ የሚል ነው።

ለአብነትም ኢትዮጵያ በሶማሌ ላንድ የባሕር በር ለመጠቀም እያደረገች ያለውን ሠላማዊ ሂደት ሞቃዲሾ እየተቃወመች ነው። ከባለጉዳይዋ ኢትዮጵያ ይልቅ ወደ ግብፅ በመመላለስ አቤቱታ እያቀረበች ነው። እውነታው ‹‹ልፋ ያለው አንድ እንጨት ያሥራል›› እንደሚባለው እየሆነ ነው።

ግብፅም ሞቃዲሾ አይዞሽ ለማለት የተጋችው አትራፊ ስለምትሆን አሊያም ጉዳዩ በቀጥታ ስለሚመለከታት ሳይሆን የ‹‹ጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው›› በሚለው ያረጀ ያፈጀ እሳቤ ነው። ይህ ከበርካቶች ውስጥ የሚጠቀስ ነጠላ ጉዳይ እንጂ፤ የኢትዮጵያ ፈተና ከዚህ በላይ ነው።

ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ታስፈልጋለች ከሚለው ነባራዊ ሁኔታ በዘለለ ኢትዮጵያም በዚህ ቀጣና ከሌሎች ቀይ ባሕር ዘላቂ በሆነ መንገድ ሠላም የመሆን ዕድል የለውም። የዓለም የፖለቲካ ፍኖታ ካርታ በየዕለቱ እየተቀያየረ ባለበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያም ከዚህ ቀጣና ማራቅ አይቻልም። ወዳጅ የበለጠ እንዲበዛ፣ ጠላትም አንገቱን እንዲደፋ በዚህ አካባቢ ቀዳሚ ሆኖ መገኘት ተገቢ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንዲሳኩ ከምኞት በዘለለ መሬት ላይ ምን መሥራት አለበት የሚለው ግን አፅንዖት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። በተለይም ደግሞ በሁሉም ዘርፍ ዲፕሎማሲን ማዕከል ያደረገ ጠንካራ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። በዚህ ዘመን የበርካቶች ቀልብ እየገዛ የመጣውን የዲጂታል ዲፕሎማሲ በተጠና መንገድ በሁለንተናዊ መልኩ መተግበር ያስፈልጋል።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከዓለም የዲፕሎማሲ እና የፖለቲካ መድረኮች ላይ ሐሳቧን የምትሸጥበት እና ቀጣናው ላይ አስፈላጊነቷን የምታጎላበት መድረኮችን በአግባቡ እና በተጠና ሁኔታ መጠቀም አለባት። ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር እና መንቀሳቀስ ደግሞ ዘመኑ የሚጠይቀው ዕውቀትና ሁኔታዎችም የግድ የሚያስብሉ ናቸው።

# ወንጀለኞችን የሚገራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሕጻን ሔቨን አወት ላይ የተፈጸመው ወንጀልና የፍርድ አሰጣጥ ሂደትስ ከሕግ ሥርዓት አንጻር እንዴት ይታያል? በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ የአስገድዶ መድፈርና የግድያ ወንጀሎችን በምን መልኩ መከላከል ይቻላል? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያነጋገርናቸው የሕግ ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

በሕገ መንግሥት ትርጉም ላይ የሚሠሩት የሕግ ባለሙያው አቶ ዓምደገብርኤል አድማሱ፣ በሀገራችን በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃቶች፣ በተለይ ሁኔታ ደግሞ በሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩና ዘግናኝ እየሆኑ መምጣታቸው የሞራልና የሥነ ምግባር መውረድ መገለጫ ነው ይላሉ። እነዚህን ወንጀሎች ለመከላከል አጥፊዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ የተሻለው መንገድ እንደሆነ የሚናገሩት ባለሙያው ይህም የመንግሥትና የሕዝብን ርብርብ እንደሚሻ ያሰምሩበታል።

በ7 ዓመቷ ሕጻን ሔቨን ላይ የተፈጸመውን ወንጀል አረመኔያዊና ዘግናኝ በሚል የገለጹት አቶ ዓምደገብርኤል፣ ከመገናኛ ብዙኃን ያገኙትን መረጃ መነሻ አድርገው፣ ዓቃቤ ሕግ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 /1/ሐ የተደነገገው የሞት ፍርድ የሚያስቀጣውን አንቀጽ እና በሕጻናት ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም በሚል የተደነገገውን በ627/1 ጠቅሶ ወንጀሉ ግዙፋዊና ተደራራቢ መሆኑን ገልጾ ክስ መስርቶ ከሆነ፣ የዓቃቤ ሕግ ክስ አመሠራረት ትክክል ነው" በማለት ይገልጻሉ። ነገር ግን፣ የወንጀሉ ግዝፈትና የፍርድ ውሳኔው ተመጣጣኝ አለመሆን ሕዝብን ብስጭት ውስጥ ከትቷል ያሉት ባለሙያው፣ ለዚህ ደግሞ መሠረታዊው ችግር ሕጉ ላይ ያለው ክፍተት መሆኑን አፅንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ በሕጻኗ ላይ የተፈጸመው ወንጀል ግዙፍና ተደራራቢ በመሆኑ ወንጀለኛው ላይ የሞት ፍርድ የሚያስፈርድ የነበረ ቢሆንም፣ የቅጣት ማቅለያን በተመለከተ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 117 በተቀመጠው መሠረት የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ እንደ ቅጣት ማቅለያ የሚታይለት መሆኑ ቅጣቱ ከሞት ፍርድ ወደ 25 ዓመት ሊያስቀይርለት መቻሉን ያስረዳሉ። የዚህ የክርክር ሂደት ችግር በቀጥታ የሕግ ክፍተት ላይ እንደሚወድቅ ያስረዳሉ።

ሌላኛው በዓቃቤ ሕግነት ለዓመታት ያገለገሉት የሕግ ባለሙያው አቶ ኢዘዲን ፈድሉ ደግሞ፣ በሕጻን ሔቨን ላይ የነበረውን የክስ ሂደት የሚገልጽ ሰነድ መመልከታቸውን ጠቅሰው፣ ዓቃቤ ሕግ ክሱን ያቀረበበት መንገድ ትክክል እንዳልሆነ ይናገራሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ ዓቃቤ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/ሀ እና 539/ ለን ተጠቅሞ የግድያ ፍርድ ማስፈረድ ይችል ነበር ይላሉ።

ወንጀሉ በግድያ መዝገብ ታይቶ ቢሆን ኖሮ መነሻ እርከኑ ሞት ይሆን ነበር ያሉት አቶ ኢዘዲን አስገድዶ መድፈር በሚለው ክስም ዓቃቤ ሕግ የተጠቀመው አንቀጽ 620 ንዑስ 3 የሕጻኗን እድሜ ታሳቢ ያደረገ ተገቢ አንቀጽ አለመሆኑንም አንስተዋል።

አቶ ኢዘዲን ልክ እንደ አቶ ዓምደገብርኤል ሁሉ የቅጣት ማቅለያ በሚል የታየለት ነጥብ በወንጀለኛው ላይ የተላለፈው የፍርድ ውሳኔ እንዲያንስ ሌላኛው ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው፣ ለወንጀለኛው የቀረበው "ምንም አይነት የወንጀል ሪከርድ የለበትም፤ የዘወትር ፀባዩ ጥሩ ነው" የሚሉ የቅጣት ማቅለያዎችን እንዲህ ያለ አሰቃቂና ዘግናኝ ወንጀል ለፈጸመ ወንጀለኛ ፈጽመው መቅረብ ያልነበረባቸው እንደነበሩ ያነሳሉ። እንደ ቅጣት ማቅለያ ቢቀርቡ እንኳ ዳኞች የቅጣት ማቅለያውን አለመቀበል ይችሉ እንደነበርም ይናገራሉ። በዚህም የፍርድ ውሳኔው ጣሪያ ዕድሜ ልክ ተደርጎ ከተወሰደ በኋላ በማቅለያው ሳቢያ አንድ እርከን ሲወርድ ውሳኔው 25 ዓመት የሚለው ላይ ሊያርፍ መቻሉን ያስረዳሉ።

የሕግ ባለሙያው፣ ሕጉ ላይ ያለው ክፍተት ግልጽ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ያለውንም ሕግ በአግባቡ ተጠቅሞ ቅጣቱ የወንጀሉን ያህል ከፍተኛ እርከን ላይ እንዳያርፍ በማድረግ ረገድ ከዓቃቤ ሕግ በኩል ግልጽ የሆነ ብቃት ችግር መኖሩን ያሳያል ይላሉ። አያይዘውም፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ሰውን የገደለ ከሆነ የቅጣት ማቅለያን የማቅረብ መብቱ መገደብ አለበት የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል።

ሕጉ ማሻሻያ ይፈልጋል የሚለው ላይ አፅንዖት ሰጥተው የሚናገሩት አቶ ዓምደገብርኤል፣ ሁልጊዜም እንዲህ ያሉ ወንጀሎች ከተፈጸሙ በኋላ የሚተላለፍ የቅጣት ውሳኔ አጥጋቢ የማይሆነው ሕጉ ላይ ባለው ክፍተት መሆኑን ደጋግመው ይናገራሉ። እንዲህ አይነት የሕዝብን ወጀብ የሚያስነሱ ጉዳዮች ሲኖሩ ሕጎችን ማሻሻል የሕግ አውጪው ተግባር ነው በማለት ያሳስባሉ።

"አንድ ወንጀለኛ ሕጻን ልጅን ደፍሮ ከገደለ ለምንድነው በሞት ፍርድ የማይቀጣው?" በማለት የሚጠይቁት የሕግ ባለሙያው አቶ ኢዘዲን ደግሞ፣ እንዲህ ላለው ወንጀል የሚተላለፈው የቅጣት እርከኑ ከፍ ማለት አለበት የሚለው ላይ ያሰምራሉ።

እንዲህ አይነት ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች የግለሰብ ሳይሆን የማኅበረሰብ ጠላት፣ የሀገር ጠንቅ ናቸው ብዬ ነው የማስበው ያሉት የሕግ ባለሙያው፣ ኅብረተሰብ ዋስትናው የተጠበቀ መሆን የሚችለው አስተማሪ የፍርድ ውሳኔዎች ሲተላለፉ ነው ይላሉ፤ እንዲህ አይነት ማኅበረሰብ እንዳይረጋጋ የመኖር ዋስትናው ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ወንጀሎች ሲፈጸሙ እንደ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል የሚል አስተያየትም ይሰጣሉ። የማኅበረሰብን እሴት የሚሸረሽሩ ወንጀሎች በሚፈጸሙበት ጊዜ የሞት ፍርድ ተግባር ላይ መዋል አለበት ነው ያሉት።

# አረንጓዴ - የሠላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ነው። ለሠላም ባለን ጠንካራ ቁርጠኝነት ይህን መሰል ተግባራት አጠናክረን እንቀጥላለን" ይላሉ።

የወይዘሮ አሚና ቃላቶች በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ፊት ላይ ከሚታየው ቁርጠኝነት ጋር ይመሳሰላሉ። ችግኞችን የመትከል ተግባር ከአካባቢያዊ ተነሳሽነት በላይ ነው። ችግኝ የወደፊት የእድገት መገለጫ ነውና ።

ለወይዘሮ አሚና እና መሰል የማኅበረሰብ አባላት እነዚህ ችግኞች የተፈጥሮ ሀብትን ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው አርሶ አደሮች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው። ማኅበረሰቡም የጥንካሬ ምልክት ነው።

ወይዘሮ አሚና አክለውም "ሁሉም ሰው የሚተከለውን ችግኝ መንከባከብ አለበት" በማለት ሌሎች በዚህ ወሳኝ ሥራ እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል። በአቅራቢያው፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ የእስልምና አባት በመባል የሚታወቁት መሐመድ ሽሪፍ፣ "ሠላማችንን እየጠበቅን የእድገት ጉዞን እያስቀጠልን ነው" በማለት፣ የዘመናት ጥልቅ ልማትና ሠላምን የመሻት ሀሳባቸውን ያጋራሉ።

"አረንጓዴው ዐሻራ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር ሥራ ነው። የሃይማኖት አባቶችም በቦታው ተገኝተው ዐሻራቸውን አሳርፈዋል። ሕዝቡ ከልማቱ ጎን ለጎን ሠላሙን እየጠበቀ ነው።" ብለዋል።

የሃይማኖት መሪዎች፣ የአካባቢ ባለሥልጣናት እና ማኅበረሰቡ ችግኞችን አንድ ላይ ሲተክሉ ማየታቸው ደስታን እንደፈጠረባቸውም መሐመድ ሽሪፍ ይገልጻሉ። ይህ ተነሳሽነት ችግኝ ከመትከል ባሻገር የመጣውን አንድነት እና የጋራ ዓላማ የሚያጎላ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

መሐመድ ሽሪፍ ማኅበረሰቡ ከዚህ ቀደም በስፋት በችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ሲሳተፍ መቆየቱን በማስታወስ፣ የዘንድሮው ግን የተለየ መሆኑን ጠቅሰዋል። "ችግኝ ሀገርን ያበለጽጋል" በማለት፣ ወጣት እና ሽማግሌ፣ ወንድ እና ሴት ሠላምን በማስጠበቅ በዚህ የለውጥ ሥራ እንዲሳተፉ አሳስበዋል።

የ75 ዓመቱ የእድሜ ባለፀጋ አቶ ይማም ኃይሌ፣ ችግኞች ሁሉም ነገር ናቸው ። እነሱ የሕይወት ሥራ መደምደሚያ ናቸው። "ዛፍ ስተክል ያለፈውን፣ የዛሬዑን እና የልጅ ልጆቼን ዕጣ ፈንታ አያለሁ። ኢትዮጵያ በታሪክ ፈተናዎች እንዳለፈች ሁሉ እነዚህ ዛፎችም ይጠናከራሉ። ያድጋሉ" ብለዋል።

ከሕይወቴ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ለሃገሬ ልማት በመሥራት አሳልፌያለሁ" የሚሉት አቶ ይማም፣ ይህ ቁርጠኝነታቸው እስከ መጨረሻው እንደሚቀጥልና ወጣቱ ትውልድም እርሳቸውን የመሰሉ ታላላቆችን በመከተል በልማቱም፤ በሠላሙም ሥራ ላይ እንዲሳተፍ መክረዋል።

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አብዱ ሁሴን (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ "ዛሬ የተተከለው ዐሻራ የነገ ብሩህነት ነፀብራቅ ነው" ሲሉ ተናግረዋል። ችግኝ መትከል የዛሬን ድህነት በአጭር ጊዜ ለመቀልበስ እና ሠርቶ የበለጠ ገቢ ለማግኘት የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ ከፍተኛ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ልማትና ሠላም እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱበት የወደፊት ምልክቶች ናቸው ያሉት አብዱ (ዶ/ር)፣ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የሕዝቡ ተሳትፎ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገር ሀገራዊ ፍቅርና ታሪካዊ ኃላፊነትን ያሳየ መሆኑን፣ መጪው ትውልድም በተመሳሳይ ስሜት የመሪነት ካባውን እንዲይዝ ማድረጉን አስገንዝበዋል።

ንጹሕ አየር እንድናገኝ አረንጓዴ ችግኝ እንደተከልን ሁሉ ለሠላም እንቅፋት የሆነውን ጽንፈኝነት የወለደውን አስተሳሰብ በንግግር በተጀመረው አግባብ በጋራ መከላከል ይገባል ነው ያሉት። ሕዝቡ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ ያደረገውን ርብርብ በማጠናከር ሠላምን ለመትከል የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ ሂደት ተሳትፎውን አጠናክሮ ማስቀጠል እንዳለበትም ነው ያሳሰቡት።

# ዲያስፖራው በሀገሩ ልማት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ዲያስፖራው ለሃገሩ ልማት በገንዘብ ከሚያደርገው ድጋፍ ባሻገር ያደጉ ሃገራትን ልምድ እና እውቀት በማምጣት እያደረገ ያለው ድጋፍ ምን ይመስላል? የሚያደርገው ድጋፍስ እንዴት ማደግ አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ የዲያስፖራ ማኅበሩን እና የሚመለከታቸውን አነጋግረናል።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ደመቀ ነጋሳ እንደሚሉት ዲያስፖራው በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሁም በማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትልቅ ተሳትፎ ያደርጋል።

በዚህም ሃገሩን ጠቅሞ እራሱም ተጠቃሚ እንደሆነ የሚገልጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በመሠረተ ልማቶች ግንባታ፣ ሆስፒታሎችን በመደገፍ የራሳቸውን ዐሻራ እያኖሩ እንደሆነ ይገልጻሉ። በቅርቡም ምሥራቅ ሐረርጌ ላይ ዲያስፖራዎች በርካታ የሕክምና ቁሳቁሶችን ድጋፍ እንዳደረጉም በአብነት ይናገራሉ።

ብዙ ዲያስፖራዎች በአደጉት ሃገራት በመማራቸው እና በመሥራታቸው እውቀት እና ልምድ ማካበታቸውን የሚገልጹት አቶ ደነቀ፤ ይህንን ልምድ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ሃገር ተጠቃሚ ትሆናለች ይላሉ።

አንዳንድ ጊዜ በሚያጋጥሙ ፖለቲካዊ ልዩነቶች ድጋፍ ማድረግ በሚችሉት መጠን የማያደርጉ ዲያስፖራዎች መኖራቸውን ተናግረው፤ አገር ሁልጊዜም ሃገር በመሆኗ የፖለቲካ ልዩነቶችን ትቶ ለሃገር የሚችሉትን ማድረግ እንደሚያስፈልግም ይገልጻሉ።

በእርሻ እና በሕክምና ዘርፍ እንዲሁም በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተሠማሩ ዲያስፖራዎች መኖራቸውን የሚናገሩት ፕሬዚዳንቱ፤ ሌሎቹም ዲያስፖራዎች ወደ ሃገራቸው በመምጣት በተለያዩ ዘርፎች በማልማት እና የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም በእውቀት እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ሃገራቸውን ማገዝ እንደሚችሉ ይናገራሉ።

የዲያስፖራ ማኅበሩ በርካታ ችግሮችን መፍታቱን የሚናገሩት አቶ ደመቀ፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር ለዲያስፖራው ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራዎች በማኅበሩ በኩል እንደሚሠሩም ይገልጻሉ።

ማኅበሩ አባላቶቹን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የማበረታታት ሥራዎችን እንደሚሠራ የሚናገሩት አቶ ደመቀ፤ ዲያስፖራው ወደ ሃገሩ ለእረፍት ሲመጣ ካለው ጊዜ አብቃቅቶ ለአጭር ጊዜ የሚመጣ በመሆኑ በመንግሥት አገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቶች ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ብዙዎች ችግር እንዳለበት የሚያነሱት በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጡ መሻሻል እንዳለበትም ይጠቁማሉ።

በርካታ ሃገራት በዲያስፖራዎቻቸው ተጠቃሚ መሆናቸውን አውስተው፤ ኢትዮጵያ በዲስፖራዎቿ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ዲያስፖራውን በሚፈለገው መጠን ማሳተፍ ያስፈልጋል ይላሉ። ዲያስፖራው በተደጋጋሚ የሚጠይቀው የሁለት አገር ዜግነት ሕግ ተሻሽሎ በሚፈልገው ልክ እንዲሳተፍ ቢደረግ መልካም መሆኑንም ይናገራሉ።

የዲያስፖራ ማኅበሩ የቦርድ አማካሪ አቶ ኤርሚያስ መኮንን በበኩላቸው እንደሚሉት ዲያስፖራው ሃገሩን በእውቀት እንዲሁም በኢንቨስትመንት ማገዝ ይችላል። ኢትዮጵያ ጥሩ የአየር ንብረት፣ ባሕል እንዲሁም ሰፊ የሕዝብ ቁጥር ያለባት ሃገር በመሆኗ ዲያስፖራዎች መጥተው ኢንቨስት ቢያደርጉ ሃገራቸውንም ጠቅመው እራሳቸውም እንደሚጠቀሙም ይናገራሉ።

ዲያስፖራው ፖለቲካዊ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ሃገርን የሚረዳበትንና የሚያሳድግበትን መንገድ በማሰብ የሞራል ግዴታም ጭምር በመሆኑ በእውቀታቸው እና በገንዘብ ለሃገር ልማት ድጋፍ በማድረግ ሃገር መለወጥ ላይ መሳተፍ አለብን ይላሉ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ወንደሰን ግርማ እንደሚሉትም የዲያስፖራው ተሳትፎ ዘርፈ ብዙ ነው። በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በኢንቨስትመንት እና በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዲያስፖራው ለሃገሩ ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሆነም ይገልጻሉ።

ባለፉት አምስት ወይም ስድስት ዓመታት በኢንቨስትመንት 30 ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ ከ500 በላይ የሚሆኑ የዲያስፖራ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተው በሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠራቸው ያወሳሉ።

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ የዲያስፖራው ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን አመልክተው፤ ከሃገር እድገት ጋር በቀጥታ ከሚገናኙት እውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ዲያስፖራው የሚታይ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን ይናገራሉ። ባለፉት ስድስት ዓመታት ከ700 በላይ የሚሆኑ የዲያስፖራ አደረጃጀቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በተለያዩ መስኮች ሥልጠናዎችን መስጠታቸውንም ይገልጻሉ።

በጤና፣ በትምህርት፣ በሰው ሀብት አስተዳደር እና በመሳሰሉት ሥልጠና እንደሚሰጡ የሚናገሩት ዳይሬክተሩ፤ የሕክምና መሣሪያዎችም ድጋፍም መደረጉን ያወሳሉ። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥም የሦስተኛ እና የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማማከር እና ኮርሶችን በጋራ በመስጠት ዲያስፖራው ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው ይላሉ። በዲጂታል ዲፕሎማሲውም በኩል ለሃገር ትልቅ እገዛ እንደሚያደርጉም ይናገራሉ።

በሪሚታንሱ ዘርፍም ዲያስፖራው ትልቅ ተሳትፎ የሚያደርግበት ዘርፍ ነው የሚሉት አቶ ወንደሰን፤ ኢትዮጵያ በየዓመቱ በአማካኝ ከ4 እስከ 5 ቢሊዮን ዶላር በሪሚታንስ እንደምታገኝ ይናገራሉ። ይህም ኢትዮጵያ ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ እንደሚበልጥም ይገልጻሉ።

የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተናግረው፤ ሪሚታንሱም እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ። የዲያስፖራውን ተሳትፎ ለማሳደግ እንደ ሃገር መሠራት ያለባቸው ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ለዲያስፖራው ትልቅ ዕድል ይዞ መምጣቱን ይገልጻሉ። ዲያስፖራው በሚኖርባቸው ሃገራት ኢንቨስተሮችን ይዞ መጥቶ በሽርክና እንዲሁም በራሱ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፍ ትልቅ እድል ከፍቷል ይላሉ።

እንደ ሃገር ከዲያስፖራው መጠቀም በሚፈለገው መጠን ጥቅም እየተገኘ እንዳልሆነ የሚናገሩት አቶ ወንደሰን፤ ኢትዮጵያ ከዲያስፖራው ማግኘት የሚገባትን እንድታገኝም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም ይገልጻሉ።

ዲያስፖራው በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በገንዘብ ለሃገሩ ድጋፍ እያደረገ መሆኑ እሙን ነው። እየተደረገ ያለው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ግን በሚጠበቀው መጠን እንዳልሆነም ተገልጿል። መንግሥት በቅርቡ ያደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለዲያስፖራው በርካታ ዕድሎችን ይዞ የመጣ በመሆኑ የዲያስፖራው ተሳትፎ እንደሚጨምር እንደሚጠበቅም ባለሙያዎቹ ሀሳባቸውን ሰጥተውበታል።

# ለሀገር የተከፈለ መስዋዕትነት

ሰሚራ በርሀ

በነበራቸው የሥራ ሥነ ምግባር ፣ በሚከተሉት የሕይወት መርህ የተግባር ሰው መሆናቸውን በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች እና የሥራ ባልደረቦቻቸው ይመሰክሩላቸዋል። ትምህርት ወዳድ በመሆናቸው የቀለም ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ በተጓዙበት መንገድ የተሰጣቸው ኃላፊነት ጥንቀቅ አድርገው መወጣትን አሳይተዋል። ከፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ እስከ ኢትዮ- ሶማሊያ ጦርነት እንዲሁም በአስመራ መድፈኛ ሆነው አገልግለዋል፤ በአስተዳደር ሥራ ውስጥም ጭምር ተሳትፈዋል። ሀገር ከፖለቲካ ልዩነትም ሆነ ከጥቅም የጸዳ ስሜት መሆን ይገባዋል ብለው ያምናሉ፤ ሻለቃ ቡሎ ኢፋ። በዛሬው የሕይወት ገጻችን ወደ ኋላ መለስ ብለው ለሌሎች አርአያ የሚሆኑበትን የሕይወት ጉዟቸውን አጫውተውናል። መልካም ንባብ ...

### ሻለቃ እና ልጅነት

ትውልዳቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር ወሊሶ ነው። እናታቸው አንጋቱ ሶቦቃ ሲባሉ አባታቸው ኢፋ ሁሉቃ በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት በጊዜው ይመሩ የነበሩ ሲሆን በአካባቢውም የሚታወቁ ናቸው። የልጅነት ጊዜያቸውን ያሳለፉበት ቤታቸው በወሊሶ ጨፎ በምትባል ቦታ የቀድሞው አርበኛ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ቤት ፊት ለፊት እንደሆነ በምናብ ያስታውሳሉ።

ለወላጆቻቸው የመጨረሻ ልጅ ሲሆኑ ኑሯቸውን በግብርና ከሚመሩት ቤተሰብ የተገኙት ሻለቃ ቡሎ ልጅነታቸው ከእርሻ ይልቅ ለቀለም ትምህርት ቦታ የሰጠ ነበር። በወቅቱ በቤተሰባቸው ዘንድ ወደ ትምህርት የገቡ ጥቂት ቢሆኑም በልጅነት አዕምሯቸው ትምህርትን በዚህ ልክ የመውደዳቸውን ምክንያትም ሲያስረዱ « ቤተሰቦቼ ባለመማራቸው ለአንዳንድ ጉዳዮች ውል ሲያጽፉ ገንዘብ ይከፍላሉ፤ መጻፍ የሚችለው ሰውም ቀጠሮ ሲያበዛባቸው በጣም ይከነክነኝ ነበር። » በማለት ለመማር ጉጉት እና ቁጭት እንዳደረባቸው ይገልጻሉ።

ሻለቃ ቡሎ በወሊሶ ከተማ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ትምህርታቸውንም ለመከታተል ችለዋል። ወቅቱ የተማሪዎች እንቅስቃሴ እዚህም እዚያም የሚቀሰቀስበት ነበርና በሚማሩበት ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የነበሩ ተማሪዎች ባነሱት አመጽ ምክንያት ለአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ከትምህርት እንዲታገዱ ተደረገ። ታዲያ ታዳጊው ቡሎ ይህንን አንድ ዓመት ቤታቸው ተቀምጠው እርሻ ማረስን አልፈለጉምና ትምህርታቸውን ለመቀጠል ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ አደረጉ።

### ጉዞ ወደ አዲስ አበባ

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ተስፋ ያደረጉት በአዲስ አበባ የሚገኙ ዘመዶቻቸውን ነበር። ነገር ግን እነርሱ የሚሰሩት በፋብሪካ ውስጥ በመሆኑ ያላቸው ገቢ ይህንን ለማድረግ እንዳልፈቀደላቸው ሻለቃ ቡሎ ያስታውሳሉ። ታዲያ በአንድ ቀን ወደ ክቡር ዘበኛ እንዲገቡ በሬዲዮ የተላለፈውን ጥሪ ያደምጣሉ። «ወደ ፖለቲካ የመግባት ምንም ፍላጎት አልነበረኝም። ነገር ግን መማር ስለምፈልግ ሠራዊቱ ውስጥ ገብቼ መማር እችላለሁ ብዬ ስላሰብኩ ክቡር ዘበኛ ውስጥ ለመቀጠር ወሰንኩ እና ወደ ጃንሜዳ ሄድኩ። » ይላሉ።

ሻለቃ ቡሎ በማንኛውም አጋጣሚ የትምህርት ፍላጎታቸውን እውን አድርገው በቀለም ትምህርታቸው መቀጠል ይሻሉ። የክቡር ዘበኛ ምዝገባቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በጊዜው አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ የፖሊስ ሠራዊት እየቀጠረ በመግቢያው ላይ በርካታ ሰዎች ተሰብስበው ይመለከታሉ፤ ጉዳዩን ለማጣራት ጠጋ ያሉት ቡሎ የነበራቸው ወጣትነትና ቁመናቸው ፖሊስ ለመሆን የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ ነበርና በአንድ የፖሊስ አመራር እይታ ውስጥ ገቡ። ከክቡር ዘበኛ ይልቅ በዚያ መቆየትን መረጡ በፖሊስ ጣቢያውም የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ሆነው ተቀጠሩ።

ወደ አዲስ አበባ የመጡት ለትምህርት ቢሆንም ነገር ግን ፖሊስ የመሆናቸው ነገር ለቤተሰቦቻቸው ለማሳመን በየጊዜው እየተመላለሱ እንደሚጠይቋቸው እና የሥራ ስምሪታቸው በተወለዱበት ቦታ ሊሆን እንደሚችል ነገሯቸው ያን ያህልም ተቃውሞ አልገጠማቸውም። በፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ሆነው ትምህርታቸውንም አስረኛ ክፍል ደርሰው መማራቸውን ቀጠሉ። ትምህርታቸውን ለመማር የመረጡት የሥራ ዘርፍ ያን ያህል የተመቸም አልነበረም። በፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ውስጥ ሳሉ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር በገጠማት ጦርነት ወደ ሶማሊያ እንዲላኩ ትእዛዝ ተሰጠ።



ሻለቃ ቡሎ ኢፋ፣

> «በዛ ጦርነት ብዙ ዜጎቻችን አልቀዋል ፣ ነገር ግን ጓደኛዬ አረፈ፤ ወገኔ ሞተ ብሎ ወደ ኋላ የሚል አልነበረም። በከፍተኛ ወኔ ነበር የምንዋጋው »

### ወደ ሶማሊያ ጦርነት ሲላኩ

ሻለቃ ቡሎ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በኦጋዴን የአስረኛ ሻለቃ ፈጥኖ ደራሽ አባል ሆነው የሶማሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ጋር በሚያዋስነው ዳር ድንበር ላይ የሚያደርገውን ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል ፤ በኦጋዴን ጎግቲ ፣ ተፈሪ በር ፤ ቶጎ ጫሌ የሚሰኙ ቦታዎች ላይ በወር ተራ እየተዘዋወሩ ድንበር የማስከበር ሥራ ከአባሎቻቸው ጋር መሥራት ጀመሩ። « ሶማሊያ ውጊያውን የከፈተችው ሐምሌ አምስት 1969 ዓ.ም በቶገ ጫሌ ላይ ነበር። ከዚያ በፊት በሰርጎ ገቦች የተለያዩ ውጊያዎች ነበሩ። ውጊያውን በመድፍ፣ በአየር በሜካናይዝድ ጦር ከፍተኛ ውጊያ አድርገዋል። » በማለት ጊዜውን ያስታውሳሉ

ውጊያውን ለመከላከል በቦታው የነበረው የእነ ሻለቃ ቡሎ ጦር የአስረኛ ብርጌድ እና የሶስተኛ ክፍለ ጦር አካል የነበረው ኃይል ውስን በመሆኑ ወደ ጂግጂጋ ተመልሶ በዚያ የመከላከል ሥራውን መሥራት ቀጠለ። ነገር ግን በጊዜው ከሶማሊያ ጦር ጋር የነበረው የኃይል መመጣጠን እጅግ አነስተኛ እንደነበር የሚያነሱት ሻለቃ ቡሎ ሆኖም ግን በሠራዊቱ ውስጥ የነበረው ወኔና ሞራል ሞት አልያም ሀገር ብለው በፍጹም ጀግንነት ሲዋጉ እንደነበር ያስታውሳሉ።

«እኛ በጊዜው የታጠቅነው የአሜሪካን የጦር መሳሪያ ነበር። የሶማሊያው ጦር ደግሞ የራሺያን ዘመናዊ ጦር በመሆኑ የማረክነውን መድፍ ወደራሳችን ቦታ ለመውሰድ ከብዶን ነበር። » ይላሉ መድፉንም የማረኩት ከጅግጅጋ ወጣ ብሎ በሚገኝ ሃሮሬሳ የሚባል ቦታ ላይ ነበር። ሻለቃ ቡሎ ጦርነቱ በይፋ ተጀምሮ ቶጎ ጫሌ ላይ ውጊያውን ሲቀላቀሉ የያዙት ላውንቸር ብቻ ነበር። ሻለቃ ቡሎ በሚዋጉበት ጦርነቱ የተጀመረው ንጋት እየተቃረበ በመጣበት ሌሊት 11 ሰዓት በኋላ በተደረገ ውጊያ ሻለቃ ቡሎ እዚያው ቶጎ ጫሌ ላይ አንድ ታንክ ማቃጠላቸውን፤ የተቃጠለው ታንክም አሁንም ድረስ እዚያው ቶጎ ጫሌ ላይ እንደሚገኝ ይገልጻሉ።

ውጊያውን ከበላይ አለቆቻቸው ጋር በመናበብና በሚሰጣቸው ትእዛዝ የሚያደርጉት ሲሆን በተሰጣቸው ትእዛዝ የነበሩበትን ምሽግ ጥለው ሲወጡ የቆሰሉ እና የተጎዱ የትግል ጓዶቻቸውን በዚያው ትተው በእጃቸው ላይ የቀረውን ቦንብ ሰጥተዋቸው ነበር ከምሽጋቸው የወጡት።

የሶማሊያ ጦር ኃይሉን አሰባስቦ ከአንድም ሁለት ጊዜ ከተማዋን ሲቆጣጠር የሻለቃ ቡሎ ጦር በካራማራ ላይ ሆኖ ይከላከል ነበር። በወቅቱ በካራማራ የምስራቅ አፍሪካን መቆጣጠር የሚያስችል ራዳር እንዳይመታ ይጠብቁ እና ይከላከሉ ነበር። ከዚያም ሁኔታው አስጊ መሆኑን ሲያውቁ በአየር ኃይል ሙያተኞች እንዲወርድ ተደረገ ይላሉ ሻለቃ ቡሎ።

«በዛ ጦርነት ብዙ ዜጎቻችን አልቀዋል ፣ ነገር ግን ጓደኛዬ አረፈ፤ ወገኔ ሞተ ብሎ ወደ ኋላ የሚል አልነበረም። በከፍተኛ ወኔ ነበር የምንዋጋው። » በማለት የነበረውን ሞራልም እንኳን ሠራዊታችን ይዋጋል መሬታችን የሚለውን መፈክር ጭምር ያስታውሳሉ።

ሻለቃ ቡሎ ወጣትነታቸው ድፍረት ፣ ለሀገር ዋጋ ለመክፈል ወደኋላ አለማለት የታጀበበት ነበር። በሶማሊያ ጦርነት ያሳለፉትን ከባድ ጊዜ ግን አሁንም ድረስ ያስታውሱታል። « ቆሬ የሚባል ቦታ ላይ ከጓደኛዬ ጋር የቀበሮ ጉድጓድ ወይንም ምሽግ እየቆፈርን ነበር። ምሽግ የሚቆፈረው ከአንገት በታች የሚቀብር ሲሆን ሶማሊያ ደግሞ በጣም በመድፍ ጥቃት በማድረስ ምሽግ ውስጥ ሆነን እንዳናየቸው ያደርጋሉ። እኛም ደግሞ የጥንቃቄ ሄልሜት አድርገን ነበር የምንቆፍረው። ሄልሜታችን ምግብ የምንሰራበት፣ ውሀ የምንጠጣበት፣ ራሳችንን ከጥይት የምንከላከልበት ነው። ምሽግ ስንቆፍር ደግሞ አፈር እንዳይበንብን እንዳንታይ የምንጠቀምበት ነው። ታዲያ በዚህ ሰዓት ድንገት የመጣ ሞርተር ጓደኛዬን ነጠቀኝ። » በማለት ከአሳዛኝ ገጠመኞቻቸው አንዱን ያነሳሉ።

ከካራ ማራ በኋላም ቆሬ የምትባል ቦታ ላይ በተደረገ ከፍተኛ መከላከል የጠላት ጦር ሰብሮ እንዳይገባ አድርገዋል። በመጨረሻም በተደረገ የኃይል ጭማሪ ካራማራን ሰብረው በመግባት የሶማሊያን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ማስወጣት መቻሉን ያስታውሳሉ ።

### የሀገር ጥሪ በአስመራ

ሻለቃ ቡሎ ቀደም ሲል በነበራቸው ሥራ በፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ውስጥ ያገለግሉ ነበር። ከዚያም በደረሳቸው የሀገር ጥሪ በኦጋዴን ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ባደረገችው ጦርነት ላይ ተሳትፈዋል። ታዲያ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ባደረገችው ጦርነት ያገኘችውን ድል ወደ ሰሜኑ ለመድገም በሚል ወደ አስመራ እንዲጓዙ ትእዛዝ ተሰጠ። ሻለቃ ቡሎ የሀገር ጥሪው ይመለከታቸው ነበርና በአዋሽ አርባ ማሰልጠኛ ውስጥ ለተወሰኑ ወራት ቆይተው የሶስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ተደራቢ የ508 ስምንት ግብረ ኃይል አካል በመሆን ወደ አስመራ አቀኑ። ወደ አስመራ በሚያደርጉት ጉዞም ጎንደር ትክል ድንጋይ ፣ ሑመራ፣ ገርገፍ፣ ጋሉች ሰብደራት የሚባሉ ቦታዎችን አቆራርጠው ባሬንቱን አልፈው ከረን የሚባሉ ቦታዎችን በእግር ማለፍ ይገባቸው ነበር። በጊዜው 147ተኛ መድፈኛ የ14ተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሻለቃ ነበሩ።

ሻለቃ ቡሎ በነበሩበት ቦታ የሠራዊቱ ትጥቅ መደራጀት አለበት በሚል በትምህርታቸው ጥሩ ደረጃ ላይ ከሚገኙት ሠራዊት ውስጥ በመምረጥ መድፈኛው እንዲደራጅ ተደረገ። በዚህም ይላሉ ሻለቃ ቡሎ ከራሺያ ሀገር የመጣ 122 ሀውቲዘር መድፍ እንዲታጠቁ ተደርጎ በውጊያው እግረኛውን እያገዙ ቆዩ። ከረን ላይ የተገናኘው ሁለት ግብረ ኃይልም በመግፋት እና በማገዝ ወደ ናቅፋ አመራ። ረጅም ጊዜ ውጊያ የተደረገበት የቀይ ኮከብ እና የባህረ ነጋሽ ዘመቻ የተካሄደበት ውጊያም ጭምር ነበር። በእነዚህ የውጊያ ጊዜያት ሠራዊቱ ከፍተኛ የሆነ የመከላከል እና የማጥቃት ሥራን የሰራው በአልጌና እና በናቅፋ ግንባር እንደነበርም ያስታውሳሉ።

ሻለቃ ቡሎ ቅጥራቸው ፈጥኖ ደራሽ ቢሆንም ከዚያ ውስጥ ለመድፈኛነት ተመርጠው የመኮንንነት ኮርስ ስልጠና በ1972 ዓ.ም በሀረር አካዳሚ ከወሰዱ በኋላ ተመልሰው በሶስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር 37ተኛ መድፈኛ ከነበሩበት ስልጠናውን ጨርሰው ወደ አስመራ ሲመለሱ የ147ተኛ መድፈኛ ሻለቃ እንዲመደቡ ተደረገ። ውጊያው እስካበቃበት ጊዜ የሻለቃ ማዕረግ እድገትን አግኝተው የአራተኛ መድፈኛ ብርጌድ የሎጀስቲክ ኃላፊ ሆኑ። በጊዜው አራተኛ ብርጌድ ማለት አስመራ የሚገኘው የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት መድፈኛ ብርጌድ ነበር።

በገጠማቸው የሀገር ጥሪ ወደ አስመራ ሲያቀኑ በተሰጣቸው ኃላፊነት ውስጥም የጀመሩትን ትምህርት በዚያም አልተውትም ነበር። በጊዜው የነበረው ሥርዓተ ትምህርት ተቀይሮ ነበርና ተስፋ ሳይቆርጡ እንደገና ከስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን መማር ጀመሩ። በጥሩ ውጤትም የስምንተኛ ክፍልን አጠናቀቁ። የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በአስመራ ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት እየተማሩ ጉብዝናቸውን ያዩ መምህር በጊዜው የሚሰጠውን ማትሪክ ፈተና እንዲወስዱ ያበረታቷቸው ነበር።


ሻለቃ ቡሎ 147ተኛ መድፈኛ ሻለቃ ውስጥ በተሰጣቸው ኃላፊነት በብዙ የሥራ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ይሰሩ ነበር። በባትሪ አዛዥነት ማለትም አራት መድፎች የያዘ አንድ ባትሪ ተብሎ ሲጠራ የዚያ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ለሀገር የተከፈለ...



ከገጽ 6 የዞረ

አራት መድፎች የያዘ አንድ ባትሪ ተብሎ ሲጠራ የዚያ አዛዥ ሆነው ይሰሩ ነበር። ከዚያም በቅርብ አለቃቸው ኮሎኔል ከበደ አማካኝነት የነበራቸውን በሳል የመሪነት ችሎታ ተገንዝበው በአስተዳደር ሥራ ላይ ሊሾሟቸው እንደሚፈልጉ ነገሯቸው።

ሻለቃ ቡሎ ግን ወጣትነታቸው ለውጊያ ለድል ያሰለጠኑትን ሠራዊት ድል ማየትን ይመኙ ነበርና ፍቃደኛ አልነበሩም። ነገር ግን የአለቃቸውን ትእዛዝ መሻር አልቻሉም ነበርና በአስመራ ጸጸራት የጦር ካምፕ ውስጥ የሚገኙ የሠራዊቱን ቤተሰብ እንዲያስተዳድሩ የሎጀስቲክስ ኃላፊ ሆነው ተሾሙ። የጦር ሰፈሩ መድፈኛ ሻለቃ መጥቶ የሚያርፍበት ተሽከርካሪዎች እና የጦር መሳሪያዎች ሲበላሹ ጥገና የሚያደርግበት እና የጦር ሠራዊት ቤተሰቡም የሚኖርበት ነው።

‹‹በጦር ካምፕ ውስጥ በግንባር ያለው ሠራዊት ስለ ቤተሰቦቻቸው በማሰብ እንዳይሰናከሉ ምክር መስጠት ፣ የወታደር ሚስቶች ወደኋላ እንዲመለሱ የሚያደርግ ደብዳቤ እንዳይጽፉላቸው መቆጣጠር እና የሠራዊቱን ልጆች መንከባከብ፣ ትምህርት እንዲማሩ ፣ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው እናደርጋለን። የተለያዩ የኳስ ትጥቆችን ገዝተን እንዲጫወቱ እናደርጋለን። ›› በማለት በጦር ካምፕ ውስጥ የነበረውን የቤተሰባዊነት ጊዜ ያስታውሳሉ። ወታደሮቹም ፍቃድ አግኝተው ቤተሰቦቻቸውን እንዲጎበኙም ጭምር ያደርጋሉ። በአስመራም ከጸጸራት የጦር ሰፈር በተጨማሪ ቃኘው የጦር ሰፈር ፣ ፎርቶ መጋላ የጦር ሰፈር የሚባሉ ነበሩ።

### ቤተሰብ መመስረት

‹‹ስፖርተኛ ነበርኩ፤ ለምንም ነገር አልሳሳም፤ ደፋር ነበርኩ›› ሲሉ የወጣትነት ጊዜቸውን የሚያስታውሱት ሻለቃ ቡሎ የትዳር ሕይወትን የመሰረቱት በአስመራ ነበር። በአስመራ ካሉ የጦር ካምፖች ውስጥ በጸጸራት የጦር ካምፕ ውስጥ የሎጀስቲክስ ኃላፊ ሆነው ከሰሩ በኋላም በኪራይ ቤቶች በዚያው አካባቢ ይኖሩ ነበር። የትዳር አጋራቸው ወላጅ አባት የምድር ባቡር ኦፕሬተር ሆነው በአስመራ ከሰልሳ አመት በላይ ቆይተዋል። ሻለቃ ቡሎም ከእሳቸው ልጅ ወይዘሮ በየነች በ1977 ዓ.ም ትዳር መስርተዋል። በአስመራ በቆዩባቸው ዓመታትም ሶስት ልጆችን አፍርተዋል። ሻለቃ ለተወሰኑ ዓመታት በአስመራ ቆይተው ሥራቸውን እየሰሩ፣ የሚወዱትን ትምህርት እየተማሩ እና ቤተሰባቸውን እያስተዳደሩ ቢኖሩም ነገር ግን ሌላ ፈተና ሳይገጥማቸው አልቀረም።

በ1983 ዓ.ም በሀገሪቱ በነበረው የኃይል ለውጥ አስመራን ለቀው ወደ ሱዳን መኳዝ የግድ ሲሆን ሲያቀኑ ቤተሰቦቻቸውን በዚያ ጥለው ነበር የሄዱት። ታዲያ ባለቤታቸው እና ልጆቻቸው ጋር በድጋሚ መገናኘት የቻሉት በቀይ መስቀል አማካኝነት ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ነበር።

### ከአስመራ ወደ ሱዳን

በጊዜው የኃይል ለውጥ በመኖሩ እና ከአቅም በላይ በመሆኑ በ1983 ዓ.ም ወደ ሱዳን ሲኳዙ ቤተሰባቸውን ትምህርታቸውን ሁሉ ትተው በቦታው ከነበሩ እና በሕይወት ከተረፉ የትግል ጓዶቻቸው ጋር በመሆን ነበር።

ጦሩም ሆነ የሠራዊቱ ቤተሰብ ይገኝበት የነበረው የጸጸራት ካምፕ ብዙውን ጊዜ የጠላት ኢላማ ውስጥ ይገባ እንደነበር የሚያስታውሱት ሻለቃ የጦር ሠራዊቱ ቤተሰቦች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ትልቅ ምሽግ በመቆፈር እና ቤተሰቡን በማሰልጠን ጥቃት ሲፈጸም ወደዚያ ምሽግ ከእነልጆቻቸው በመግባት ሊተርፉ ችለዋል።

በ1983 ሻዕቢያ የጦር የበላይነትን ይዞ ወደ አስመራ ሲጠጋ የአራተኛ መድፈኛ ብርጌድ የሎጀስቲክ ኃላፊ የሆኑት ሻለቃ ቡሎ ከፍተኛ የጥይት ዲፖ የነበረበትን ቦታ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች እና ጥይት ለማንሳት ቢሞክርም ሙለ ሙሉ ለማንሳት ግን አልተቻለም። በፍጹም ጠላት እጅ መግባት የለበትም የሚሉት ሻለቃ ቡሎ በወሰዱት አፋጣኝ ርምጃ በቲኤንቲ ከፍተኛ ፈንጂ በጠቅላላ እንዲወድም አድርገዋል። ጦርነቱን ለማሸነፍ በጊዜው ከእስራኤል ሀገር የመጣ የድምጽ ቅኝት መሳሪያ እንደነበር የሚያስታውሱት ሻለቃ ‹‹መሳሪያው የመጣው በስውር ነበር። 46 የመኪና ባትሪ ነበር የሚያንቀሳቅሰው። ባትሪዎቹን የሚሞላ ሁለት የራሱ ጀኔሬተር ያለው እና የራሱ ሪሞት ኮንትሮልም ነበረው። ሲመጣም ከአውሮፕላን የተቀበልኩት እኔ ነበርኩ። መድፍ ከየት እንደተተኮሰ የሚነግር ጨረር የሚለቅ ነበር። ጠላት እጅ እንዳይገባ ከእስራኤል ሀገር በሚስጥር ነበር የመጣው›› መሳሪያውን ለመጠቀም ከምድር ጦር እና ከአየር ኃይል ተመርጠው ወደ እስራኤል ሀገር ሄደው ስልጠናውንም ወስደዋል።

በኋላም መሳሪያውን ለመጠቀመው የሚያስችለውን ሪሞት የተላከው በአንድ ባለሙያ በኩል ከእስራኤል ሀገር ወደ ምድር ጦር ነበር። ‹‹መሳሪያውን ኦፕሬት ለማድረግ የሰለጠነው ባለሙያውም ሪሞቱን ለማምጣት ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ተላከ። ሪሞቱን ይዞ ወደ አስመራ መምጣት ነበረበት። ግን ከአሜሪካ የመጣች እህቱ ተመልሰህ ወደ ውጊያ አትገባም በማለት ይዛው ከሀገር ወጣች። ›› በማለት የሚያስታውሱት ሻለቃ ቡሎ መሳሪያው በአስመራ ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት አጠገብ የነበረ ራዳር ቦታ ላይ ቆሞ ነበር። ውጊያው እልባት የሚያገኝበት የመጨረሻ ሰዓት ነበርና መሳሪያውን መጠቀም ባለመቻሉ ሻለቃ ቡሎ ይህ መሳሪያ በፍጹም ጠላት እጅ አይገባም በማለት በዚያው ቦታ እንዲወድም አደረጉት። ያጊዜም የጦርነቱ ማብቂያ ነበርና ሕይወታቸውን ለማትረፍ ወደ ሱዳን ጉዟቸውን አደረጉ። ቤተሰቦቻቸውን ትተው ለባለቤታቸውም ‹‹ቻው ደህና ሁኚ በሕይወት ከቆየሁ እንገናኛለን ፤ ካልተገናኘንም ልጆቼን አደራ ›› የሚለው ቃላቸው ነበር።

ከአስመራ ወደ ሱዳን በእግራቸው ሲያቀኑ የሎጀስቲክስ ኃላፊ ነበሩና የጥገና ክህሎትም ነበራቸው። ታዲያ በአስመራ ባዶሮ የሚባል ቦታ ላይ ያገኙትን የተበላሸ መኪና አስተካክለው የተወሰነ ጉዞ አድርገው ወደ ሱዳን ከሚሄደው ጦር ጋር መቀላቀል ቻሉ። በእግር ባደረጉት ረጅም ጉዞ ከረን ከደረሱ በኋላ ከዚያም አቆርደት ላይ ጦሩ ተሰባስቦ በጊዜው በነበሩ የሥራ ኃላፊዎች አቀናጅተው ነዳጅ ያላቸውን መኪኖች የጦር መሳሪያዎችን እየያዙ ነዳጅ ያለቀባቸውን ደግሞ የማቃጠል ትእዛዝ ተሰጠ።

ሻለቃ ቡሎ የመድፈኛው ብርጌድ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው መሪዎችን እያጀቡ እና ጥቃት እንዳይደርስባቸው እየተከላከሉ ተሰኔ ከዚያም አሊግደር አንድ ቀን አደሩ። በዚያ ቆይታቸው አዲስ አበባ ከሚገኙት ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ነዳጅ እና ቀለብ እንዲላክላቸው ጠየቁ። የተሰጣቸውን መልስ ግን ባላቸው ሠራዊት ባላችሁ ነዳጅ እንደምንም ሆናችሁ ወደ ሀገራችሁ ግቡ የሚል ነበር። ነገር ግን የነበራቸው ትጥቅ እና አቅም ወደ ሀገራቸው የሚያደርስ አልነበረምና በቦታው በነበሩ ጄኔራሎች ባደረጉት ውይይት ወደ ሱዳን እንዲገቡ የሚጠይቅ ልዑክ ተላከ።

‹‹ከሱዳን መንግሥት ጋር በመደራደር መሳሪያችንን ጥለን መድፎች ወደኋላ ታንኮች ቱሬታቸውን ወደኋላ አዙረው ያለንን መሳሪያ እያስቀመጥን እንድንገባ ትእዛዝ ተሰጠን። ከዚያም ሱዳን ከሰላ አቦ ጊመል የሚባል ቦታ ላይ እንድንገባ ተፈቀደልን። ›› ወደ ሱዳን ለመግባት በተፈቀደላቸው ጊዜ መሳሪያቸውን እንዳራገፉ የተከሰተው ክስተት ሲያነሱ አሁንም ድረስ ስሜታቸው ይረበሻል። ‹‹ መሳሪያችንን ጥለን ወደ ሱዳን ስንገባ የሻዕቢያ ጦር ተዘጋጅቶ ነበርና መሳሪያቸውን ባወረዱ ጦረኛ ተዋጊዎች ላይ ኃይሉን ማሳየት ጀመረ። ምንም መሳሪያ ባልያዘ ወታደር ላይ ሠራዊቱን ረሸኑ፤ የቀረውም ሠራዊት ሕይወቱን ለማትረፍ ወደ ሱዳን ገባ። ›› በማለት በፍጹም ሊደረግ የማይገባው ተግባር እንደነበር ያነሳሉ።

በፖርት ሱዳን ወደ 460 የሚጠጉ መኮንኖች ቆይተው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ጥያቄ አቅርበው በተደረገ ውይይት ከሶስት ወራት ቆይታ በኋላ ሀምሌ 27 ቀን ወደ አዲስ አበባ ገቡ።

### በድጋሚ ቤተሰባዊነትን ስለመቀጠል

የሻለቃ ቡሎ ባለቤት ባላቸው የት እንዳለ እና እንደደረሰ አያውቁምና የአንድ ዓመት፣ የአምስት ዓመት የሰባት ዓመት ህጻናት ልጆቻቸውን ይዘው ወደ አዲስ አበባ እንደመጡ ልጆቻቸውንና የባለቤታቸውን ፎቶ ይዘው የሻለቃ ቡሎ ወላጆች ወሊሶ አቅንተው የልጅ ልጆቻቸውን አስተዋወቁ። ነገር ግን በጊዜው የሻለቃ ቡሎ ወላጆች የልጃቸውን በሕይወት መኖር አልያም ማረፍ ማወቅ አልቻሉም ነበር።

በሱዳን ያረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከዛሬ ነገ ወደ ሀገር ቤት ይመለሳል የሚል ዜና በቴሌቭዥን ጣቢያ ይተላለፍ ነበርና የሻለቃ ቡሎ ባለቤት የሌሎች ሠራዊት ቤተሰቦች በየቀኑ ወደ አየር ማረፊያ በመሄድ ቤተሰቦቻቸውን ለማግኘት ይጠባበቁ ነበር። ‹‹ ወደ ሀገሬ እንደገባሁ ባለቤቴ ልጆቼ የት እንዳሉ አላውቅም ነበር። እናም አየር ማረፊያ እንደደረስኩ ስሜ ሲጠራ ባለቤቴ እና ልጆቼን ሳያቸው ፍጹም ስላልጠበቅኩ ቃላት ለማውጣት እንኳን ተቸግሬ ነበር። ›› ሲሉ ሻለቃ ቡሎ ያን ጊዜ ያስታውሱታል።

ሻለቃ ቡሎም ወደ ሀገራቸው ገብተው ወደ ጦላይ ማሰልጠኛ እንዲሄዱ ሲደረግ በፊት እግረ መንገዳቸውን በሕይወት መኖራቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ለቤተሰቦቻቸው ሲጽፉ ባለቤታቸው መጥተው እንደጠየቋቸው እና የልጅ ልጆቻቸውን መተዋወቃቸውን ከወላጆቻቸው መልዕክት ሲደርሳቸው የደስታ እና የሀዘን ስሜት በእኩል ሰዓት ያስተናገዱበት ጊዜ እንደነበር ሻለቃ ያነሳሉ።

### ተሀድሶ ኮሚሽን

ሻለቃ ቡሎ ወደ ሀገራቸው እንደገቡ ወቅቱ የኃይል ለውጥ ተደርጎ ሀገሪቱን ይመራ የነበረው የኢህአዴግ መንግሥት ነበርና የተሀድሶ ስልጠና ለመውሰድ ወደ ጦላይ ማሰልጠኛ እንዲገቡ ተደረገ። ሻለቃ ቡሎ ይህንን ስልጠና ከመውሰዳቸው አስቀድሞ ከአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ጀምሮ ሀገራቸውን በውትድርና ለ20 ዓመታት ያህል አገልግለዋል። በጦላይ የተሀድሶ ስልጠና ሲወስዱ የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አስተዳደር ኃላፊ አድርገው መረጧቸው። የተሀድሶ ስልጠናቸውን ከጨረሱ በኋላ በሠራዊቱ ውስጥ እንዲቀጥሉ ጥያቄ ቀረበላቸው። ሻለቃ ቡሎ ግን የሲቪል ሕይወትን መቀላቀል መረጡ ‹‹ በሶማሊያ ጦርነት በጣም ብዙ ውጣ ውረድ አሳልፈያለሁ፣ ወጣትነቴን ሰጥቻለሁ፤ በልጅነቴ ያፈራሁትን ሀብት ጭምር አጥቻለሁ፤ እድሜዬም እየገፋ በመሄዱ መቀጠልን አልፈለኩም ነበር። ›› የሚሉት ሻለቃ ቡሎ በወጣትነታቸው የነበራቸውን ደፋርነት በሶማሊያ ጦርነት ያሳለፉት ሰቆቃ ፊታቸውን ላይ ድቅን እንደሚል ይገልጻሉ።

### ሌላ የሕይወት ምዕራፍ

ከፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጀምረው ወጣትነታቸውን ወኔቸውን የሰጡለት ሙያ የሀገር ሠራዊትን የተቀላቀሉበት ወቅት የተሳተፉበት ጦርነት ለሀገር ትልቅ ውለታን የዋለ የውትድርና ሥራ ሙያ ውስጥ ለ20 ዓመታት አገልግለዋል። በጥልቅ የሀገር ፍቅር ስሜት እና ቀላል የማይባሉ በጊዜ ሂደት እንኳን ሊረሱ የማይችሉ ከባድ እና የጀግንነት ጊዜን አሳልፈዋል። በወጣትነት ጊዜያቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ሲመሩ ሻለቃ የሚል ማዕረግን አግኝተው መልካም የሥራ ጊዜን አሳልፈዋል።

ሻለቃ ቡሎ የሲቪል ሕይወትን ከመረጡ በኋላ የተሰማሩት በታክሲ ሥራ ላይ ነበር። ወታደር በባህሪው ካለው የልብስ መለዮ ጨምሮ የራሱ ግርማ ሞገስ በህብረተሰቡም ዘንድ የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነውና እንዴት የታክሲ ሥራን መረጡ ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ስለሥራ ክቡርነት ያላቸውን ሃሳብ በዚህ መልኩ ገልጸውልናል። ‹‹አንድ የማምንበት ነገር በክረምት ወቅት የሠርግ ጥሪ ቢኖር ወደ ተጠራበት ቦታ ጸኣዳ ልብስ ለብሶ የሚሄድ ሰው ድንገት ጭቃ ላይ ቢወድቅ እዛው አይቀርም። ልብሱን እንደምንም አጽድቶ ወደ ተጠራበት ሠርግ ይሄዳል። ›› የሚሉት ሻለቃ ቡሎ ለዓመታት የቆዩበት የውትድርና ሕይወት ያስተማራቸው ጥንካሬን በሥራ ክቡርነት እንዲያምኑ ዝቅ ብሎ መሥራት ምንም ማለት እንዳልሆነ ኃላፊነትን እስከ መጨረሻው መወጣት ምን እንደሚመስል ያሳዩበት ነው።

የሲቪል ሕይወትን ሲቀላቀሉ የጀመሩት የታክሲ ሥራ ለስድስት ዓመት ያህል ከሰሩ በኋላ ሥራው በሚያሳድረው ጫና በገጠማቸው የኩላሊት ህመም አማካኝነት ሥራቸውን አቁመው ወደሌላ የግል ሥራ ገቡ። ይህም ቤተሰቦቻቸውን ለማስተዳደር እና እሳቸውን መርጣ ወላጆቿን ጥላ በጋራ ያፈሯቸውን ልጆች ለምታሳድግ ሚስት እና እናት እንደ አንድ ኃላፊነት እንደሚሰማው አባትና አባወራ ለቤተሰባቸው ሊከፍሉት በደስታ የተቀበሉት መስዋዕትነት እንደነበር ሻለቃ ቡሎ ይገልጻሉ። ‹‹ምንም ጤናዬ ቢጎዳም ልጆቼን አሳድጊያለሁ፤ አስተምሬያለሁ፤ በሰራሁት ሠራም ረክቻለሁ ምንም የሚቆጨኝ ነገር የለም። ›› ይላሉ። ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ካላቸው ፍላጎት የተነሳም ትምህርታቸውን ትተው ሕይወትን ማሸነፍ ለቤተሰብ መኖር ላይ አተኩረዋል ።

የታክሲ ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላም በሌላ የግል ድርጅት ውስጥ በሱፐርቫይዘር ፣ ሳይት ጥናት ስምሪት እና በአስተዳደር ሥራ ለ12 ዓመት ያህል ሰርተዋል። በቤተሰብ ሕይወታቸውም አምስት ልጆችን የወለዱ ሲሆን የልጅ ልጅም አይተዋል።

### እድሜ የሚያስተምረው

ባሳለፉት ሕይወት በነበራቸው ስብዕናና እና የሥራ ሥነ-ምግባር ጓደኞቻቸው ምሳሌ እንደሚያደርጓቸው ይናገራሉ። በውትድርና ዓለም ውስጥ ትልቁ መርህ ሁል ጊዜም ዝግጁ መሆን እና ጽናት መሆኑን የሚያነሱት ሻለቃ ቡሎ ኢፋ አሁን ላይ እድሜያቸው ሰባ ዓመት ሲሆን ይህ ትውልድ መማር ያለበት ይላሉ።

‹‹ የዛሬ ልጆች አንድ ችግር ሲገጥማቸው ቶሎ ይበሳጫሉ። ችግርን እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው አያውቁም። የሥራ - ሥነ ምግባር፣ ዝቅ ብሎ መሥራት እና ረጋ ማለትን ማወቅ አለባቸው። ምክንያቱም ነገም ሌላ ቀን ነው። ይሄ ለልጆቼም ጭምር ሁሌ የምላቸው ነው። ›› በማለት ወጣቱ በትንሽ በትልቁ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለበት ይመክራሉ።

ሻለቃ ቡሎ ይህን የሚሉት በበረሀ በውጊያ ላይ ሳሉ ከቤተሰቦቻቸው ከልጆቻቸው መራቃቸው ጎድቷቸው ስሜታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው ራሳቸውን ያጠፉ እንዳሉ በማስታወስም ጭምር ነው።

# ባህልና ቱሪዝም

## የወርሃ ነሐሴ የሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ድምቀቶች

**ዳግም ከበደ**



የበጋው ወር አልፎ ክረምት ሲገባ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ከተፈጥሮ ጋር ያለው ወዳጅነት ይጠብቃል። ከጋራ ሸንተረሩ፣ ከሜዳ ጉድባው ጋር መነጋገር ይጀምራል። ከዝናቡ፣ ከማጡ፣ ከብርድና ቁሩ ጋር ይፋለማል፡፡

የሰብል እርሻውን አለስልሶ በዘር ይሸፍናል፣ የጓሮ አትክልቱን፣ የፍራፍሬ እፅዋቱን ይተክላል። የክረምት ወቅት ለኢትዮጵያ አርሶ አደር እጅጉን አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ለመላው ኢትዮጵያውያንም ልዩ ትርጉም አለው። የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ዋናው መሠረት የሆነው ይህ የግብርና ወቅት ከሀገሪቱ ዓመታዊ የግብርና ምርት አብዛኛው የሚመረትበት ነው፡፡

በሐምሌና ነሐሴ ከሚደረገው ጠንካራው የእርሻ ሥራ ጎን ለጎን ይህ ወቅት ደማቅ የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶች የሚንፀባረቁበትም ነው። ጎብኚዎች ወደ ገጠራማው የኢትዮጵያ ክፍል ቢያቀኑ ከማራኪ የግብርና ሥራው ባሻገር በክረምት ከሚገለጠው የተፈጥሮ ፀጋ ጋር ተገናኝተው የማይረሳ ትዝታን ሸምተው ይመለሳሉ።

ኢትዮጵያውያን ከመስከረም እስከ መስከረም በባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት የሚደምቁ የዓለም ፈረጦች ናቸው። ሀገሪቱ የብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ እና የብዝሀ ሃይማኖትና ባሕል መገኛ እንደመሆኗ መጠን የማህበረሰቡን እሴት የሚወክሉ፣ የመላውን ዓለም ቀልብ የሚስቡ ደማቅ ክብረ በዓላት ዓመቱን ሙሉ ይከናወኑባታል። ከእነዚህ በርካታ መስህቦችና ሀብቶች መካከል ደግሞ የክረምቱን ወር (በተለይ ነሐሴን) ጠብቀው የሚከበሩ ተወዳጅ ክብረ በዓላት ይገኛሉ።

በወረሃ ነሐሴ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የሚያከብሩት ጾመ ፍልሰታ ተከትሎ ሁለት በዓላት በድምቀት ይካሄዳሉ። እነዚህ በዓላት በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል። በዓላቱ የደብረ ታቦር (ቡሄ) እና የልጃገረዶች በዓል የሆነው አሸንድዬ፣ አሸንዳና የሶለል ባሕላዊ ጨዋታዎች ናቸው።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር መረጃ እንዲሁም የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች እንደሚጠቁሙት፤ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች የሚገኙበት የሻደይ/አሸንዳ ክብረ በዓል ‹‹የሴቶች የነፃነት በዓል እንደሆነ የሚታመን፤ በክብረ በዓሉ ወቅት በተለይ ልጃገረዶች እንደልባቸው በመሆን በነጻነት የሚጫወቱበትና በአደባባይ ደምቀው የሚታዩበት ነው›› በማለት ተወዳጁን ባሕላዊ ሥርዓት ይገልፁታል።

የዝግጅት ክፍላችንም በዓሉ ከፆመ ፍልሰታ ፍቺ ቀን አንስቶ እስከ መስከረም ወር እየተከበረ የሚቆይ ተወዳጅ መስህብ እንደመሆኑ መጠን የአከባበር ሥነ ሥርዓቱን፣ ለኢትዮጵያውያን ያለውን ትርጉም እንዲሁም የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በባሕላዊ ሥርዓቱ ላይ ያደረገውን ጥናታዊ ዳሰሳ ጨምሮ የተለያዩ መረጃዎችን ለመቃኘት ወዷል፡፡

ወይዘሮ ነፊሳ አልማህዲ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ ጥበብ ሥነ ጥበብ ፈጠራ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው። እርሳቸው የዘንድሮውን የአሸንድዬ፣ ሻደይ፣ አሸንዳና ሶለል ክብረ በዓላትን አስመልክተው አንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ እንደየ ብሔር ብረሰቦችና ሕዝቦች ባሕልና ወግ፣ የአኗኗር ሥርዓትና ፍልስፍና ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የምታስተናግድበት እምቅ የሆነ የባሕል ባለቤት ሀገር ነች።

ከነዚህም በዓላት መካከል የሴቶች የነፃነት ቀን እንደሆነ የሚነገርለት የአሸንድዬ፣ ሻደይ፣ አሸንዳና ሶለል የሴቶች በዓል አንዱ ሲሆን፣ ሴቶች በጉጉት፣ በናፍቆት፣ በፍቅርና በልዩ ዝግጅት የሚጠብቁትና በሚኖሩበት ማህበራዊ ሥርዓት ሥነልቦናዊ እርካታ የሚያገኙበት ደማቅ በዓል ነው። በበዓሉ ወቅት ሴቶች እውቀታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ፈጠራቸውን፣ ችሎታቸውን፣ ልምዳቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ፍልስፍናቸውን እንዲሁም መፃኢ ተስፋቸውን የሚያዩበትና የሀገር በቀል የምስጋና ባህርይ የሚስተዋልበት በዓል ጭምር ነው።

ሚኒስቴር ዴኤታዋ እንዳስረዱት፤ ሀገር በቀልና ጥንታዊ ባሕሎቻችን ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ በማንነቱ የሚኮራና ባሐላዊ ሀብቶቹን አውቆና ተረድቶ በራሱ የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር የአሸንድዬ፣ ሻደይ፣ አሸንዳና ሶለል የሴቶች በዓልን ጨምሮ በብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውስጥ ያሉ ቱባ ባሕሎችን ለመጠበቅ፣ ለማጥናት፣ ለማልማት፣ ለማደራጀትና ለማስተዋወቅ ሁሉም የየራሱን ድርሻ መወጣት ይገባዋል።

የሴቶች የነፃነት ባሕል ተደርጎ የሚቆጠረው በዓል ከሚከበርባቸው የሰሜኑ ክፍል አካባቢዎች አንዱ የሰቆጣ ከተማ ይገኝበታል። በአካባቢው የሚከበረው ይህ ባሕል ሻደይ የሚል ስያሜ አለው። የከተማዋ ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ የሆኑት አቶ መላሽ ወርቃለም እንደሚገልፁት፤ ባሕላዊ ትውፊቱን፣ ወጉንና እሴቱን በጠበቀ መልኩ በዋግ ሹሞች መናገሻ በሰቆጣ ከተማ በድምቀት ለዘመናት ሲከበር ቆይቷል። ዘንድሮም በተመሳሳይ መልኩ እየተከበረ ይገኛል።

‹‹የሻደይ በዓል ምንም እንኳን የልጃገረዶች በዓል ቢሆንም እንደ ማህበረሰብ ብዙ ትርጉም አለው›› የሚሉት ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባው፤ ከልጃገረዶች ባሕልና የነፃነት ቀን ባሻገርም ዘመድ ከዘመድ ጋር የሚጠያየቅበት፣ በዋግ ሕዝብ ውስጥ ትልቅ ማህበራዊ መስተጋብር የሚፈጥር ተወዳጅ በዓል መሆኑን አስታውቀዋል። ይህን የማህበረሰብ ባሕላዊ ሥርዓትም ከትውልድ ወደ ትውልድ ጠብቆ ለማሸጋገር እንደሚሰራም ተናግረዋል።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አባይ መንግሥቴ በበኩላቸው ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ ላይ እንደተናገሩት፤ በያዝነው በነሐሴ ወር ደማቅ ሥርዓትን የያዘው የሴቶች የነፃነት የሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል በዓል እንዲሁም የቡሄ፣ እንግጫ ነቀላና ከሴ አጨዳ በዓል እንደ ከዚህ ቀደሙ በደማቅ ሁኔታ እየተከበረ ነው።

የአማራ ክልል ከአስደማሚ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ በተጨማሪ የጎብኝዎችን ቀልብ የሚስቡ ዓመቱን ሙሉ የሚከበሩ በርካታ ባሕላዊ ክብረ በዓላት መኖራቸውን አቶ አባይ በመግለጫቸው አንስተዋል። ከእነዚህ ክብረ በዓላት መካከል በያዝነው የወርሀ ነሐሴ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በድምቀት የሚከበሩት የሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ቡሄ፣ እንግጫ ነቀላና ከሴ አጨዳ ይገኙበታል ሲሉ እሳቸውም ተናግረዋል። ክብረ በዓላቱ በየአካባቢዎቹ እየተከበሩ እንደሚቀጥሉ የሚያነሱት አቶ አባይ፣ በተለይም ሻደይ በዋግ ኽምራ፣ አሸንድዬ በላስታ ላሊበላ፣ ሶለል በራያ ቆቦ፣ ከሴ አጨዳና እንግጫ ነቀላ በምስራቅ ጎጃም የሚከበሩ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሚከበረውን የልጃገረዶች በዓል በታላቅ ድምቀት ከሚያከብሩት መካከል የትግራይ ብሔረሰብ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዓሉ በክልሉ አሸንዳ በሚል ይታወቃል። የዘንድሮው የአሸንዳ በዓልም ባሕላዊ ሥርዓቱን ጠብቆ እየተከበረ መሆኑን የክልሉ መንግሥት ኮሚኒኬሽን እና መገናኛ ብዙሃን አሳውቀዋል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ‹‹የአሸንዳ በዓል በትግራይ፣ ዋግ ኽምራና ላስታ-ላሊበላ›› በሚል በጥናት መልክ ሰርቶ ይፋ ባደረገው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ እንደተመለከተው፤ በዓሉ በትግራይ አሸንዳ በሚል በየዓመቱ በወርሀ ነሐሴ በክልሉ ርዕሰ ከተማ በመቐለ፣ በእንደርታ፣ አዲግራት፣ ተምቤን ጨምሮ በልዩ ልዩ አካባቢዎች ይከበራል።

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ያካሄደው ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚጠቁመው፤ የአሸንዳ በዓል በየዓመቱ ከነሐሴ 16 እስከ 21 ባለው ጊዜ ውስጥ ለአንድ ሳምንት ያህል ሲከበር የቆየና ዛሬም እየተከበረ የሚገኝ ነው፡፡ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በዓሉ የበለጠ እውቅና እንዲያገኝና የሁሉም በዓል ሆኖ እንዲከበር በመደረጉ በአደባባይ በፌስቲቫል መልክ ከነሐሴ 16-18 ባለው ጊዜ ለሶስት ተከታታይ ቀናት በመቐለ፣ በዓብዓዲ/ተምቤን፣ በአዲግራት እንዲሁም በአክሱም ነሐሴ 24 ቀን በድምቀት እየተከበረ የሚገኝ ታላቅ ክብረ በዓል ነው፡፡

እንደ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ጥናታዊ ማብራሪያ፤ የአሸንዳ በዓል በሚከበርበት ወቅት ልጃገረዶች ተወዳጅ የሆነውን ጨዋታቸውን በባሕላዊ አልባሳት ደምቀው ይጫወታሉ። ልጃገረዶች እንደ የቡድናቸው አለባበሳቸውን፣ የአሸንዳ ቅጠል አስተሳሰራቸውን፣ የአንገት ጌጦቻቸውን፣ የጸጉር አሰራራቸውን ሁሉ እርስ በርስ አስተካክለው፣ አምረውና ተውበው ለጨዋታው ዝግጁ እንደሚሆኑም ይገልፃል፡፡

በዚህ መልኩ ዝግጅታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከተለያየ አቅጣጫ ግንባራቸውን በእጃቸው ያዝ ቀና እያደረጉ ለጨዋታው እንዲሰባሰቡ ከጓደኞቻቸው ጋር በዚህ ወቅት በሚደረግ የአጠራር ዘይቤ መሰረት በድምጽ ይጠራራሉ፡፡ ከበሯቸውን እየመቱና እየዘፈኑ ወደጋራ የመሰብሰቢያ ቦታቸው በመውጣት ክብ ሰርተው ጨዋታቸውን ይጀምራሉ፡፡ አሸንዳም በዚህ መልኩ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ያልፋል። በዚህ መሰል ፌስቲቫል ላይ ለመሳተፍ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ወደ ትግራይ ክልል እንደሚያቀኑም መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በሰሜኑ በልዩ ድምቀት ከሚከበረው የልጃገረዶች በዓል ውስጥ ሻደይ አንዱ መሆኑን ጠቅሶ፣ ታሪካዊና ባሕላዊ መሰረቱን እንዲህ እንደሚከተለው ያብራራል። የሻደይ ክብረ በዓል /ባሕላዊ ጨዋታ/ አከባበር የሚጀመረው በወርሃ ነሐሴ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ክብረ በዓሉ የፍልሰታ ጾም በሚፈታበት ነሐሴ 16 ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ የሚከወን መሆኑን አብራርቶ፣ የአከባበር ሥርዓቱ በአለባበስ፣ በአጊያጌጥ፣ በቡድን ምስረታና በመሳሰሉት የራሱ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶችና ቅድመ ሥርዓቶች እንዳሉት ጠቁመዋል፡፡

ሻደይ የክረምት ወቅት /ወርሃ ነሐሴ/ ምድር ከከባድ ዝናብ መላቀቅ የሚጀምርበት፣ ሜዳው፣ ሸንተረሩ፣ ሸለቆና ተራራው በዓመት አንድ ጊዜ ብቅ በሚለው የአደይ አበባ የሚያጌጥበትና የምድር አዝዕርትም ፍሬ ማፍራት የሚጀምሩበትና የክረምቱ መልካምነት የሚረጋገጥበት ወቅት በመሆኑ ቀደም ባሉት ጊዜያት በዓሉ መከበሩ አምላክ ከአለፈው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን በሰላም፣ በፍቅር፣ በጥጋብ ለመሸጋገሩ ምስጋና በብሔረሰቡ የሚቀርብበት እንደሆነ ይታመናል በማለት የበዓል አከባበሩን ዳራ ያስረዳል፡፡

በአማራ ክልል የልጃገረዶች በዓል አሸንድዬ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት እንደሚከበር የቅርስ ባለስልጣን ጥናታዊ ጽሑፍ ይጠቁማል። ክብረ በዓሉ ማህበረሰቡ ማንነቱን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ ወግ፣ ቋንቋና ባሕል እንዳለው የሚያሳይበት መሆኑንም ያስረዳል።

የላስታ-ላሊበላ ሕዝብም በየደረሰበት የዘመን ምዕራፍ ሁሉ ደስታውንና ብሶቱን የሚገልጽባቸው የብርቅዬ ባሕሎች ባለቤት መሆኑን በመጥቀስም በየዓመቱ ከሚከናወኑ በርካታ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ጨዋታዎች መካከል ‹‹አሸንድዬ›› አንዱና ዋናው የአካባቢው ማህበረሰብ መገለጫ መሆኑን ያስረዳል፡፡

የአሸንድዬ ባሕላዊ ጨዋታ በአካባቢው ማህበረሰብ በየዓመቱ በጉጉት ተጠብቆ መከበሩ የአካባቢው ህብረተሰብ በራሱ ባሕል እንዲኮራ ከማስቻሉም በላይ ባሕላዊ ጨዋታው ታሪካዊነቱ እንዲጠበቅና ከትውልድ ወደትውልድ እንዲሸጋገር ያስቻለው መሆኑን መረጃ ያብራራል፡፡ ላስታ ላሊበላ ቱሪስት የሚጎርፍበት መካነ ቅርስ በመሆኑም ክብረ በዓሉ ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር የራሱ ድርሻ ያለው እሴት መሆኑንም ይጠቁማል።

### እንደ መውጫ

እንደሚታወቀው የዓመቱ መገባደጃና የመስከረም መባቻ በሆነው ወርሀ ነሐሴ ላይ እንገኛለን። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ተወዳጅና ማራኪ የሆኑ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥርዓቶችን የምታከብርበት ማህበረሰቡም በባሕላዊ እሴቶቹ የሚደምቅበትና የሚዋብበት ነው። የደብረ ታቦርና አሸንዳ አሸንደዬ በዓላት ለመስከረም አቀባበል የሚያደርጉ፤ መጪውን ዘመን በብሩህ ተስፋ እንድንቀበል መሠረት የሚሆኑን ፈርጦችም ናቸው። ነገር ግን በዓላቱን ከዚያም በላይ ትርፍ አላቸው።

እነዚህ ተወዳጅ እሴቶች ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላይ የማስተዋወቅ፤ በቱሪዝም ዘርፍ የኢኮኖሚና የሀገር መልካም ገፅታን የመገንባት እድል የሚፈጥሩ ናቸው። በመሆኑም በዓላቱ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ፣ እንዲለሙና ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጣቸው የሚመለከታቸው አካላት ተግተው እንዲሰሩ የዝግጅት ክፍላችን ለማሳሰብ ይወዳል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# የአፍሪካ እግር ኳስ አባት

**ዋስልኝ አየለ**

ስሙ የሚነሳው በታሪክ ለማስታወስ ብቻ አይደለም። በዜና እና በእግር ኳስ ትንተና ፕሮግራሞች ውስጥ ሁሉ ስሙ ይነሳል። ድል የራቀው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ‹‹በእሱ ጊዜ ቀረ›› ለማለት ይመስላል የስፖርት ጋዜጠኞች የዚህን ሰው ስም በተደጋጋሚ ያነሳሉ። ይድነቃቸው ተሰማ እሸቴ!

እግር ኳስን ተጫውቶታል፣ እግር ኳስን አሰልጥኖታል፣ እግር ኳስን በብቃት መርቶታል። በእግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ስሙ ተደጋግሞ ይነሳል። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 37 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ነሐሴ 13 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየንን የይድነቃቸው ተሰማን ዝርዝር ታሪኮች እናስታውሳለን። ለዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውሳለን።

ከ82 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 13 ቀን 1934 ዓ.ም ‹‹የሰማዩ ጠላቂ፣ የሰማዩ ቀዛፊ...›› እየተባሉ የሚጠሩት፤ በሶማሊያ ወረራ ጊዜ የዚያድ ባሬን የጦር አውሮፕላን አየር ላይ ዶግ አመድ ያደረጉት፤ የአየር ኃይሉ መሃንዲስ ብርጋዴር ጄኔራል ለገሠ ተፈራ ተወለዱ። የዚህን ጀግና ታሪክ በመስከረም ወር በዝርዝር ማስታወሳችን ይታወሳል።

ከ120 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 14 ቀን 1896 ዓ.ም ከፋሺስት ጣሊያን ጋር ከፍተኛ ውጊያ አድርጎ፤ በተለይም በአንዱ የጦር ሜዳ የጠላትን አውሮፕላን በእሩምታ ተኩስ እንዲወድቅ አድርጎ ድል ያስመዘገበው፤ በአጠቃላይ በፋሽስት ጣሊያን የወረራ ሙከራ ወቅት የሀገርን ክብር ያስጠበቀው ስመ ጥሩ አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ ተለወደ። የራስ አበበ አረጋይን ዝርዝር ታሪክ በተለያዩ አጋጣሚዎች በዝርዝር ማስታወሳችን ይታወሳል።

ከ12 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 14 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የአቶ መለስ ዜናዊን የሕይወት፣ የትግልና የአመራር ዝርዝር ታሪኮች ባለፈው ግንቦት ወር ማስታወሳችን ይታወሳል።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የይድነቃቸው ተሰማ ታሪክ እናልፋለን።

ይድነቃቸው ተሰማ መስከረም 1 ቀን 1914 ዓ.ም ጅማ ከተማ ውስጥ ተወለደ። አባቱ የበርካታ ሙያዎች ባለቤት የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ሲሆኑ እናቱ ደግሞ ወይዘሮ ሙላቷ ገብረሥላሴ ይባላሉ። አዝማሪ፣ ባለቅኔ፣ ቀራፂ፣ ሰዓሊ፣ ነጋዴ፣ መካኒክ፣ ፖለቲከኛ፣ ፎቶ አንሺ ... የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ፤ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ፣ በልጅ ኢያሱ፣ በንግሥት ዘውዲቱና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥታት ስመ ጥር ሰው ነበሩ። በተለይ በልጅ ኢያሱ ዘመን ጉልህ ፖለቲካዊ ተሣትፎ ነበራቸው። ከዚህ በተጨማሪም ለልጅ ኢያሱም የተለየ አክብሮት ስለነበራቸውና አብዛኛው በአዲስ አበባ ከተማ የነበረው የመሐል ሀገሩ መኳንንት ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ በተሰለፈ ጊዜ ሁሉ፤ ነጋድራስ ተሰማ ግን የልጅ ኢያሱ ታማኝ ባለሟል ሆነው እስከ መጨረሻው ድረስ በመዝለቃቸው ልጅ ኢያሱ ከሥልጣናቸው ተሽረው ዘውዲቱ ምኒልክ ንግሥት፤ ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ደግሞ አልጋ ወራሽ ሆነው በተሾሙበት ወቅት በቀልድ አዋቂነታቸውም ተደናቂ የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ፣ በግዞት ወደ ጅማ ተወስደው ነበር። ይድነቃቸው የተወለደው በዚህ ወቅት ነው።

ይድነቃቸው እንደማንኛውም የዘመኑ ልጆች እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የቄስ ትምህርት ቤት ገብቶ የመጽሐፍ ቅዱስ እና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ተምሯል። የፈረንሳይኛ ትምህርትን ደግሞ በአሊያንስ፣ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች ተከታትሏል። በወቅቱም ለእግር ኳስ፣ ለብስክሌትና ለሩጫ ስፖርቶች ልዩ ፍቅር ነበረው። ብስክሌቱንና ሩጫውን ባይገፋበትም እግር ኳሱን ግን በተጨዋችነት፣ በአሠልጣኝነትና በኋላም በአመራርነት እስከሕይወቱ ፍፃሜ ቀጥሎበት ዛሬም ድረስ ስሙን ማስጠራት የቻለበት ስፖርት ሆኖለታል። ገና በስምንት ዓመቱ የትምህርት ቤቱ የሕፃናት እግር ኳስ ቡድንን በአምበልነት እየመራ ተጫውቷል። በ1924 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴና የስዊድኑ ንጉሥ ልጅ በተገኙበት መድረክ ይድነቃቸውና የትምህርት ቤት ጓደኞቹ የስፖርት ትርዒት አቅርበው ሽልማት ተቀብለዋል።

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ይድነቃቸው ወደ ኢጣሊያ ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት በወቅቱ ለሀገር ተወላጆች (ለኢትዮጵያውያን) ይሰጥ የነበረውን ትምህርት አጠናቋል። ይድነቃቸው በ1928 ዓ.ም ወደ ፈረንሳይ ለመሄድ ከተመረጡት ሁለት ጎበዝ ተማሪዎች መካከል አንዱ በመሆን ዝግጅቱን አጠናቅቆ የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያ በፋሺስት ኢጣሊያ በመወረሯ ምክንያት የፈረንሳዩ ጉዞው ሳይሳካ ቀረ።

በስምንት ዓመት ዕድሜው የስፖርት ዓለም ተሳትፎን የጀመረው ይድነቃቸው፣ በ14 ዓመቱ የአራዳ ልጆች የነበሩት አየለ አትናሽ እና ጆርጅ ዱካስ የመሠረቱትን የዛሬውን ‹‹ቅዱስ ጊዮርጊስ›› የእግር ኳስ ቡድንን ተቀላቀለ።

በወቅቱም እነይድነቃቸው ጨዋታዎችን ሲያደርጉ የግብ አግዳሚና ቋሚ እንጨቶችን ተሸክመው በየቦታው ይንከራተቱ ነበር። የግብ አግዳሚና ቋሚዎችን በቋሚነት መትከል ደግሞ የሚሞከር አልነበረም። ሌላው ሁሉ ይቅርና ‹‹ሳር ታበላሻላችሁ›› በሚል የሚደርስባቸው ተቃውሞ እንኳ ከባድ ነበር።

ይድነቃቸው ለ23 ዓመታት ያህል ለቅዱስ ጊዮርጊስ ተሰልፎ በመጫወት ለክለቡ ለረጅም ዓመታት በመጫወት እስካሁን ድረስ ባለ ክብረወሰን ነው። ከይድነቃቸው በመቀጠል ለቅዱስ ጊዮርጊስ ለብዙ ጊዜያት የተጫወተው ለ16 ዓመታት ያህል ቡድኑን ያገለገለው ዝነኛው ተጫዋች መንግሥቱ ወርቁ ነው።

በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ይታተም የነበረውና ‹‹የሮማ ብርሃን›› የተሰኘው ጋዜጣ በወቅቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከስድስት ኪሎ ቡድን ጋር ያደረገውን ጨዋታ በዘገበበት ጽሑፉ የይድነቃቸውን ብቃት እንዲህ ሲል ገልፆት ነበር።

«… ነገር ግን ስድስት ኪሎዎች ምንም እንኳ በራቸውን አጠንክረው ይዘው ቢጫወቱም ኳሲቱ ዙራ ዙራ ከዚያው ከይድነቃቸው እግር ገባችና ይድነቃቸው እንደልማዱ ኳሲቱን ይዞ ከፊት ያገኘውን ልጅ ሁሉ እያሳለፈና እያስዘለለ ሲሮጥ ኳሲቱ በገዛ እጅዋ የምትሮጥ ትመስል ነበር እንጂ እሱ በእግሩ የሚነዳት አይመስልም ነበር ...»

ይድነቃቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ በቆየባቸው ዓመታት ከተጫዋችነት በተጨማሪ አሠልጣኝ ሆኖም አገልግሏል። በአንድ የውድድር ዘመን ለክለቡ 43 ግቦችን ማስቆጠር ችሏል። ይህ ስኬትም ይድነቃቸውን እስካሁን ድረስ ባለክብረወሰን አድርጎታል። ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንም ተሰልፎ ተጫውቷል።

ይድነቃቸው የተጫዋችነት ዘመኑን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ አሠልጣኝነት በመሸጋገር የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድንን መርቷል። ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ አንድ ለእናቱ የሆነውን የአፍሪካ ዋንጫዋን (1954) ስታሸንፍ የቡድኑ አሠልጣኝ ይድነቃቸው ነበር። ኢትዮጵያ ባለድል የሆነችበት የሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር የውድድሩ ከፍተኛ ኮከብ ግብ አስቆጣሪዎችም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አምበሉ ሉቺያኖ ቫሳሎ እና የግብፁ አብደልፋታህ በደዊ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ሦስት ግቦችን አስቆጥረዋል። የውድደሩ ኮከብ ተጫዋች ሆኖ የተመረጠው ደግሞ ዝነኛው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቹ መንግሥቱ ወርቁ ነበር።

ይድነቃቸው ተሰማ ከተጫዋችነትና ከአሠልጣኝነታቸው ባሻገር ታላላቅ ተግባራትን ያከናወኑትና ታዋቂነትን ያተረፉት የስፖርት ማኅበራትን በማደራጀትና በመምራት ነው። የኢትዮጵያ ስፖርት ጽሕፈት ቤትን አቋቁመው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ጥረዋል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ሲመሰረትም አስተዋፅአዋቸው እጅግ የጎላ ነበር። በወቅቱም የፌደሬሽኑ ዋና ፀሐፊ ሆነው ተመርጠው ነበር።

በ1949 ዓ.ም የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (CAF) አህጉራዊ ውክልና ኖሮት በዓለም እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ማኅበር (FIFA) ውስጥ እንዲሳተፍ ታቀደ። ኮንፌደሬሽኑ በየካቲት 1949 ዓ.ም በካርቱም ከተማ ተመሠረተ። በምስረታ ስብሰባው ላይም አቶ ይድነቃቸው ኢትዮጵያን በመወከል ተገኙ። በወቅቱ የተሻለ አቅም የነበረውን ፌዴሬሽን የመሠረተችው ግብጽ የማህበሩን ጽሕፈት ቤት ወደ ካይሮ ከተማ እንዲዛወር አድርጋ ግብፃዊው ኢንጂነር አብደልአዚዝ አብደላ ሳሌም የመጀመሪያው የኮንፌደሬሽኑ ፕሬዝደንት ሆነው ተሾሙ። ከመስራቾቹ በመቀጠልም ደቡብ አፍሪካ እና ሌሎች ሀገራት ታዳጊውን ተቋም በአባልነት ተቀላቀሉ። ከድርጅቱ ምስረታ ጀርባ የይድነቃቸው ሚና የጎላ ነበር። የኮንፌደሬሽኑን መተዳደሪያ ደንብ በመቅረጽ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው። ይድነቃቸው ይህንኑ ኮንፌደሬሽን፣ እ.አ.አ ከ1964 እስከ1972 በምክትል ፕሬዝደንትነት፣ ከ1972 እስከ 1987 ደግሞ በፕሬዝደንትነት መርተውታል።

ይድነቃቸው በደቡብ አፍሪካ ይካሄድ በነበረው የአፓርታይድ ሥርዓት ላይ በሚያሳዩት ተቃውሞም ይታወቁ ነበር። የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ሲጀመር የደቡብ አፍሪካ እግር ኳስ ማህበር « ... ‹ሁሉም ጥቁር› አልያም ‹ሁሉም ነጭ› የሆኑ ተጫዋቾች እንጂ በምንም



**ይድነቃቸው ተሰማ፣**

አይነት ሁኔታ ‹ከሁለቱም የተዋሀደ› ቡድን ወደ ውድድሩ አልክም ...›› ማለቱን ተከትሎ ይድነቃቸውን ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች የእኩልነት መብት ተሟጋቾች ደቡብ አፍሪካ ከአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን እንድትገለል ጫና በማሳደራቸው እ.አ.አ በ1958 ካፍ ደቡብ አፍሪካን ከአባልነት አገዳት። በወቅቱ የይድነቃቸው የሥራ ባልደረባና የካፍ ተወካይ የነበሩት አብድልሐሊም መሐመድ ደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ፖለቲካዊ ሥርዓቷን በስፖርት ውስጥ እንዲንሰራፋ በማድረጓ ካፍ ከአባልነት ሲያግዳት በይድነቃቸው የማያወላውል ጽኑ አቋም ምክንያት እንደነበር መስክረዋል።

ከቅኝ ግዛት ተላቅቀው ነፃነታቸውን የሚጎናፀፉ የአፍሪካና እስያ ሀገራት ቁጥር መጨመር ዘረኝነትን የተከተለ አሠራርን የሚተገብሩ ሀገራት ከዓለም አቀፉም ሆነ ከአህጉራዊ ማኅበራት እንዲታገዱ ጫና ማሳደሩን አጠናከረው። ይህም በወቅቱ ለዘረኛ አሠራሮች ጥብቅና ቆመው የነበሩ የፊፋ አመራሮችን ከፍተኛ ጫና ውስጥ ከተታቸው። ከአፍሪካ፣ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካ እና ሶቭየት ኅብረት በተገኘ ሰፊ ድጋፍና በጊዜው የካፍ ምክትል ፕሬዝደንት አቶ ይድነቃቸው መሪነት የፊፋ ምክር ቤት ደቡብ አፍሪካ ላይ በድጋሚ የእገዳ ውሳኔ አሳለፈ።

በዓለም ዋንጫ ውድድር ላይ የነበረው የአፍሪካውያን ኮታ እንዲስተካከል እነአቶ ይድነቃቸው በፅናት መከራከራቸውንም ቀጠሉ። የወቅቱ የፊፋ ፕሬዝደንት የነበሩት ስታንሊ ሮውስ

‹‹ ... ብዙ ሰዎች ተጨባጭ ያልሆነ ሃሳብ እንደሆነ ያምናሉ። ለምሳሌ እንደ እንግሊዝ ያለች እግር ኳስ የተጀመረባትና ምስረታውን ያደራጀች ሀገር ወይም ደግሞ ሰፊ ልምድ ያላቸው፣ በፊፋ ምስረታ ወቅት ትልቅ ድርሻ የነበራቸው እንዲሁም በዓለም እግር ኳስ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ችግሮች ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጣልያንና ፈረንሳይን የመሳሰሉት ሀገሮች ከአፍሪካና እስያ ከሚመጡ ሀገሮች ጋር እኩል ድምፅ የመስጠት መብት መኖር የለበትም ...›› ብለው አስተያየት ሰጡ። አቶ ይድነቀቻውም በዚህ የሮውስ የማን አለብኝነት አመለካከት ተገርመው ‹‹... ምንም እንኳ ለፊፋ መመሥረት የተወሰኑ አህጉራት በተቋሙ የእድገት ሒደት ውስጥ በሃሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ ረገድ ያበረከቱትን የተሻለ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ብንረዳም እኛ የምንጠብቀው ግን ተቋሙ ዓለምአቀፋዊ ድርጅት የመሆኑን ያህል በዴሞክራሲያዊ አሠራር የሁሉንም አባል ሀገራት መብቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያስከብር እንዲሆን ነው። ስለዚህም አሠራሩ በሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የዓለም እግር ኳስን ጥቅምና አንድነትን በዘላቂ ሒደትን የሚከተል እንዲሁም በፊፋ ወስጥ ያሉት አባላት በሚያድግ ሚዛናዊ ውክልና እንዲሳተፉ መደረግ አለበት ...›› ሲሉ ሞገቱ። አቶ ይድነቃቸው ‹‹አንድ ሀገር አንድ ድምጽ›› የሚለውን የምክር ቤቱን መመሪያ በስኬታማነት ከመታገላቸውም በላይ በሮውስ አመራር የዓለም ዋንጫ አውሮፓን ማዕከል ባደረገው ንፍቀ ክበብ ብቻ ተወስኖ እንዳይዘልቅና ለሌሎች አህጉራትም እንዲዳረስ ረጃጅምና ተከታታይ የደብዳቤ ግንኙነቶችን ከሮውስ ጋር በማድረግ አፍሪካ የቀጥታ ተሳትፎ ኮታ ኖሯት እግር ኳሷ እንዲበረታታና እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። በዚህም ስኬታማ ነበሩ።

የአፍሪካን እግር ኳስ ጥቅምና ፍላጎት በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስጠበቅ ረገድ የአቶ ይድነቃቸው ሚና እየጎለበተ ሄዶ ኃላፊነታቸውም ጨመረ። እ.አ.አ በ1966 ዓ.ም የፊፋ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል፣ በ1967 የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ እንዲሁም በ1972 ዓ.ም ደግሞ የካፍ ፕሬዝደንት ሆነው ተሾሙ። በአንደበተ ርቱዕነታቸው የሚታወቁት አቶ ይድነቃቸው ከጥሩ አማርኛ ተናጋሪነታቸው በተጨማሪ እንግሊዝኛን፣ ፈረንሳይኛን እና ጣልያንኛን በጥሩ ሁኔታ መናገር መቻላቸው በዓለም አቀፍ ስፖርት አስተዳደር መድረኮች ውስጥ ያለውን ውስብስቡን ፖለቲካ በአፍሪካ የእንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ተናጋሪ ማዕዘናት በተሟላ ክህሎት ለማሰስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶላቸዋል።

እ.አ.አ በ1974 ብራዚላዊው ዥያን ማሪ ፎስቲን ጎድፍሮይድ ጆኣዎ ዴ ሃቨላንጅ (‹‹ጆ ሃቨላንጅ››) የፊፋ ፕሬዝደንት ሆነው ተመረጡ። ወቅቱ አቶ ይድነቃቸው የካፍ ፕሬዝደንት ሆነው ማገልገል የጀመሩበት ጊዜ ነበር። አፍሪካም በ1960ዎቹ ስትታገልላቸው ለነበሩት ዓላማዎቿ ግልጽ ድጋፍ የሚያደርግ የእግር ኳስ መሪን እ.አ.አ በ1970ዎቹ አጋማሽ አገኘች። ካፍ ቀደም ሲል ከፊፋ ጋር ባለመስማማቱ ይፈጠሩ የነበሩ ከውድድሮች ራስን የማግለል እና ከባለስልጣናቱ ጋር የሚደረጉ እልህ አስጨራሽ ትግሎች ቀርተው የአፍሪካን ግቦች ማሳካት ተጀመረ። እ.አ.አ በ1974 በፍራንክፈርት በተካሄደው የፊፋ ስብሰባ ላይ የጎሳ፣ የዘር እና የሃይማኖት መድልዎን በሀገሩ ውስጥ የሚያሰፍን ማንኛውም የፊፋ አባል ሀገር ከዚህ ድርጊቱ የማይታቀብ ከሆነ ፈጣን የእገዳ ውሳኔ እንዲተላለፍበት ካፍ ሃሳብ አቀረበ። ደቡብ አፍሪካም ከፊፋ አባልነቷ ተባረረች። በዓለም ዋንጫ የሚሳተፉ የአፍሪካ ተወካዮች ቁጥርም አደገ።

አቶ ይድነቃቸው በካፍና በፊፋ ውስጥ ከነበራቸው የሥራ ኃላፊነት በተጨማሪ የአፍሪካ ስፖርት ኮንፌደሬሽኖች ኅብረት ፕሬዝደንት፣ የአፍሪካ ብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮሚቴዎች የክብር ፕሬዝደንት እንዲሁም የአፍሪካ ስፖርት ጠቅላይ ምክር ቤት እና የዓለም አቀፍ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አባል ሆነውም አገልግለዋል።

ከሦስት አሥርት ዓመታት በፊት ጋዜጠኞች ለወቅቱ የፊፋ ፕሬዝደንት ጆ ሀቨላንጅ ‹‹ከእርስዎ በኋላ የፊፋ ፕሬዝደንት ማን ይሆናል? እርስዎን የሚተካው ማነው?›› ብለው ሲጠይቋቸው ባጭር ቋንቋ ‹‹ሚስተር ተሰማ ነዋ!›› በማለት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ለቦታው እንደሚመጥኑ ተናግረው ነበር።

ሃቨላንጅ ያለምክንያት አልነበረም እኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ የስፖርትና የኦሊምፒክ ግንባር ቀደም መሪን ለትልቁ የኃላፊነት ቦታ ያጯቸው። አቶ ይድነቃቸው የኢትዮጵያን ዘመናዊ ስፖርት ያደራጁ፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴን ትክክለኛ መስመር ያስያዙ፣ ለአፍሪካ ብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮሚቴዎች ማኅበር ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ለብሔራዊ ኢሊምፒክ ኮሚቴዎች ማኅበር ህልውና የተጉ፣ ልዩ ልዩ ሕጎችንና መተዳደሪያ ደንቦችን በአማርኛ ያዘጋጁና ለአፍሪካም የተረፉ ታላቅ ሰው ናቸው። አቶ ይድነቃቸው ተሰማ፣ ዘርንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረገን የስፖርት ክለቦች አደረጃጀትን በጥብቅ ያወግዙና ይቃወሙ ነበር። ከዚህ ባሻገር በስፖርታዊ ክንውኖች ወቅት የሲጋራና የአልኮል ምርቶች በስታዲየሞች አካባቢዎች እንዳይተዋወቁ በፅናት ይከራከሩም ነበር።

ታዲያ ሃቨላንጅ ያኔ አቶ ይድነቃቸውን ለፊፋ ፕሬዝደንትነት ሲያስቧቸው ለጥቆማቸው አክብሮታቸውን የገለፁት ታላቁ ኢትዮጵያዊ፣ በጤና እክል ምክንያት እጩነቱን ለመቀበል እንደሚቸገሩ ተናግረዋል። የበርካታ ሪከርዶች ባለቤት የሆኑት አቶ ይድነቃቸው፤ ከውጭ ሀገራት መንግሥታት ሳይቀር ብዙ ዋንጫዎችን፣ ሜዳሊያዎችንና ሌሎች ሽልማቶችን አግኝተዋል።

በእርግጥ አቶ ይድነቃቸው የአፍሪካ እግር ኳስ የወደፊት አቅጣጫን በሚመለከት ከፍተኛ የሆነ ሃሳብ ነበራቸው። እ.አ.አ በ1974 ዓ.ም በተካሄደው የካፍ ስብሰባ ላይ ‹‹ ... በዚህ ጠቅላላ ጉባዔ አፍሪካ አንድ እና የማትከፋፈል መሆኗን በማረጋገጥ፣ የአፍሪካን አንድነት ለማስጠበቅ በጋራ እንድንሠራ፣ በእግር ኳሳችን እና በአጠቃላይ የኑሮ ገጽታችን ላይ የተንሰራፋውን ባዕድ አምልኮ፣ ጎሰኝነትና ሌሎች የምንገለልባቸውን ነገሮች በሙሉ እንድናወግዝ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ ...›› በማለት ተናግረው ነበር።

# የዝነኞች ገጽ

# አወዛጋቢው ደራሲ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ጎሩይ የማን ነው? ንጉሤስ ከወዴት አለ? አውግቸውስ ማነው?... ሁሉንም ፈልጎ አንዱን ከማግኘት፣ አንዱን ፈልጎ ሁሉንም ማወቅ ይቀላል። ይኼ አንዱ፤ ይህ እርሱ ብዕርን በእጁ ብቻ ሳይሆን በልቡም ጭምር የሚጨብጥ አንድ አውታታ ምስኪን ደራሲ ነው። በሥራው የሚያስደምም፣ በስምና ኑሮው የሚያወዛግብ፣ ብዕሩ የማይነጥፍ፣ ልቡም የማይነትብ ታላቅ ደራሲ ነው። አንዳንዴ ሕይወቱንም ጭምር የሚደርስ ይመስላል። ከጎጃም ተነስቶ አዲስ አበባ፣ ከቤተክርስቲያን ወደ ጎዳና፣ ከቅኔ እስከተሰበረ የሕይወት መቅኔ፣ ከመርካቶ እስከ...እያለ በመጽሐፍት ሻጭነትም፣ ከ20 በላይ መጽሐፍትን እስከመጻፍ የበቃም ደራሲ ነው።

በሥራዎቹ ካልሆነ በስተቀር በስም ጠርቶ ስለ እርሱ ለማውራት ሳያዳግት አይቀርም። ምክንያቱም ስሞቹም እንደሥራዎቹ በየአቅጣጫው፣ በየፊላው ስርና በየፊናው የተከማቹ በመሆናቸው ነው። አንዳንድ በእርግጠኝነት ሚዛን ያልተለኩትን እንኳን ብንተው ለአብነት የሚሆኑ ሦስት ስያሜዎች አሉት። ገና ሲወለድ ወላጆቹ የሰየሙትና የሚያውቁት "ንጉሤ ሚናስ" በሚል ነበር።

ቀጥሎ ደግሞ በሁለተኛነት "ጎሩይ ሚናስ" ያወጡለት እጅግ የሚወዱት አንድ አጎቱ ቢሆንም በዚህ ስም ሲጠሩት የነበሩም ቀላል አይደሉም። ከእነዚህ ሁሉ በኋላ የመጣው "አውግቸው ተረፈ" የተሰኘውን ስሙን እንኳን በኑሮ መሃል ድንገት ለራሱ የሰየመው ስም እንጂ የትውልድ ቀዬው በዚህ አያውቀውም። በአንድ ወቅት መርካቶ ውስጥ ብዙዎች የሚፈልጉት መጽሐፍ ሻጭ ነበር። ወደ አውግቸውነት የተለወጠው የዚህን ጊዜ ራሱን ሲያስተዋውቅ ነበር። የኋላም የብዕር ስሙ ይኼው ሆነ።

እንግዲህ ስለእርሱ በስም ከማውጋት ይልቅ በሥራው ማውሳት ሳይቀል አይቀርምና "ወይ አዲስ አበባ" የሚለውን መጽሐፍን እንጥቀስ...እስቲ ታዲያ ከአውግቸውና "ወይ አዲስ አበባ" ከሚለው ማንስ ነው ታዋቂ? ማንስ ነው ዝነኛ? ከባለቤቱ ይልቅ መጽሐፉ፣ ከሠሪው ይልቅ ሥራው፣ ከአናጢው ይልቅ ብርኩማው ዝነኛ ነው ላለማለት አይቻልም። እንግዲህ በዚያም ሲሉ በዚህ ንጉሤ የሚሉት ስሙ ሳይነግስ ቀረና የመጠሪያውን ዙፋን በአውግቸው ተረፈና በጎሩይ ሚናስ ተያዘ።

ዛሬ ዝናውን እንድናነሳለት ያደረገን በሥራው ነውና ምን ሠርቶ...እንበል። ደራሲነት፣ ተርጓሚነትና አርታኢነት መታወቂያዎቹ ናቸው። በድርሰት ሥራው ከፍ ተደርጎ የሚነገርለት "ወይ አዲስ አበባ" እና "እብዱ" የተሰኙት የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ የሆኑ መጽሐፍቶቹ ናቸው። የመጀመሪያውን በ1979ዓ.ም ሁለተኛውንም በ2002ዓ.ም አስነብቦ አድናቆትን ተቀብሎባቸዋል። "እነ ወተቴ"፣ "የሙኒት ምርጫ"፣ "ኒኒ በርጋጊዋ"፣ "ማሞ ቢጩ"፣ "ስለሺና ስምንተኛው ሺ"፣ "ሁለት ሌሊት ከዲያቢሎስ ጋር" የሚሉትን መጽሐፍቶች በመሃል ሲያስነብብ ቆይቷል። ግራ ቀኙ እያለ ደግሞ ጋዜጣና መጽሔቶችንም አስሷል። "ኒኒ በርጋጊዋ" በዚሁ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጽፎ በማስነበብ በሰዓቱ እጅግ ተወዳጅ የሆነለት ሥራው ነበር።

በመጽሔቶች ላይም እየጻፈ በርከት ያሉትን ምርጥ ጽሁፎችን አስነብቧል። በርከት ያሉ የውጭ መጽሐፍትን በመተርጎም ከራሱ ሥራዎች ባልተናነሰ ገኖባቸዋል። በዚህ ሥራውም ያገኘው አድናቆት፣ ያካበተው ዝና ቀላል አይደለም። ለትርጉም ሥራው የመጀመሪያ የሆነችው "ያንገት ጌጡ" ስትሆን ቀጥሎም የሄኔሪ ባልዛክን "ሚስኪኗ ከበርቴ"፣ የሀርሎድ ሮቢንሰን "ባይታወር" እና "ጩቤው"፣ የሲዲኒ ሺልደን "ደመኛው ሙሽራ" የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው።


ከሕይወት ጨለፍታ...ፊታችንን ወደ ውልደትና ትውልድ ቀዬው አሻቅበን ከተመለከትን ሥፍራው ወደ ብዙ ዕውቅ ደራሲያን ወንዝ ያሻግረናል። የተወለደው በ1943ዓ.ም ሲሆን የተወለደውም በጎጃም፣ ከጎጃምም በቢቸና አውራጃ ውስጥ ነበር። ልጅ ሆኖ በጎጃም አሉ በተባሉ አብያተ ቅኔያት ሁሉ ዞሯል። ስንብት...ዳዊት...ድጓ...ብቻ ከሁሉም ጠግቦ በልቷል። በዚያን ጊዜ እንደ ሚፈጽመው ግብሩ ቢሆንማ ኖሮ እንደ ወላጆቹና እንደቀዬው እሳቤ ሁሉ ጳጳስ አሊያም ቄስ፣ ዲያቆን አሊያም ሰባኪ ወንጌል በሆነ ነበር። ግን አልሆነም...የያኔውን በንጉሤነቱ የተመኙለትንና ያዩለትን ወደፊታቸውን ትቶ ወደ ፊቱን ፍለጋ ወጣ። ያየውን እየተከተለ ደራሲውን አውግቸውን ለመሆን በ1960 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ።

"ወይ አዲስ አበባ" ያለው የዚህን ጊዜ ይሆን... ገና እንደመጣ ከመንፈሳዊው ዓለም ወጥቶ ወደ ውጭ አልተመለከትም።"ቀጨኔ መድኃኔዓለም ገባሁና አልስማማ ሲለኝ ቀጥሎ ወደ ቅድስተ ማርያም ሄድኩ። በዚያም አንድ ጓደኛዬን ስላገኘሁት ዝም ብዬ ከዚያው ለአንድ ዓመት ተቀመጥኩ። የተማሪዎች ማደሪያ ስለነበረ ቅዳሴ እንማራለን ብለን ተመልሰን ገባን። እየተማርን በመሃል እናቋርጥ ስለነበረ ከዚያም አባረሩን" ሲል በአንድ ወቅት በአንደበቱ ተናግሮ ነበር። እናም ከዚህ መባረር በኋላ ነበር የበረንዳ አዳሪ ሆኖ የውጪዋን አዲስ አበባን የተዋወቃት። ከጓደኛው ጋር ሆነው ቁራሽ እንጀራና ፍርፋሪ እየተመገቡ በመጽዋቹ ቸርነት ለስድስት ወራት ያህል ዘለቁ።

የጎዳናው ሕይወት ለ17 ዓመቱ አውግቸውና ጓደኛው እጅግ አስከፊና እንግዳ ነበር። ኑሮን በእንዲህ ለመዝለቅ እንደማይቻል እየገባቸው በየግላቸው ያብሰለስሉት ነበር። እናም አንድ ሌላ የሕይወት መንገድ የግድ ነበር። ዓይናቸውን ወዲህና ወዲያ እየወረወሩ በየፊናቸው አዲስ ሕይወት ፍለጋ ያማትሩ ጀመር። አውግቸው ከነበረበት ጎዳና ተራምዶ በቀጥታ ወደ ጡረታ ሰፈር ሄደ። አንድ ተስፋ የሚሆነውንም ነገር አገኘ። ከአንድ ልበ ብርሃን ጋር ተገናኝቶም እርሱን እየመራ ወደሚፈልገው ቦታ ሁሉ ማድረስ እንደ ሥራ ገባበት። ትንሽዬ ሳንቲም እየተከፈለውም ከዚሁ ሰው ጋር ለሁለት ዓመታት ተቀመጠ። ማየት ላልቻለው ዓይን እየሆነለት ሲመራውና የገባበት ገብቶ ሲወጣ ከተማዋን ከእግር እስከ ራስ ከማወቅም ከሰዎች ጋር መተዋወቁንም አትርፎበታል። እንደገና ሌላ የተሻለ ዕድል አገኘ። አለቃ ነብዩ ልዑል የተባሉ አንድ ሌላ ልበ ብርሃንን እየመራ በወር 12 ብር ይከፍሉታል። አለቃው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ስለነበሩ የግላቸው ቢሮም ነበራቸውና የአውግቸው ሥራ እጅ ይዞ በመምራቱ ላይ ብቻ አልቆመም። ያነብላቸዋል። የሚፈልጉትንና የሚሉትንም ይጽፍላቸዋል። የሚሉትን መጽሐፍ እየፈለገ፣ ከሚፈልጉት ቦታ ላይ ያገላብጥላቸዋል። ከእኚህ ሰው ጋር እንዲህ ባለ መልኩ የዘለቀው ለአንድ ዓመት ብቻ ቢሆንም፤ ምናልባትም ግን ትልቁን የሕይወት መዳረሻ መሠረት ያኖረው በዚህን ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከዚህ በኋላ አውግቸው እንደገና ከፍ ያለበትን ሌላ የሕይወት አጋጣሚ ተገናኘ። በጓደኛው ጥቆማ ተቀጥሮ ወደ መጽሐፍት ንግድ ገባ። ሕይወቱን መጽሐፍቱን በመሸጥ ሳይገታ ትምህርቱን የመማር ሃሳብ በራለት። ቀን ቀን መጽሐፍ በመሸጥ ሲኳትን ውሎ ማታ ማታ ደግሞ ካቆመበት 3ኛ ክፍል ትምህርቱን ቀጠለ። ቀጥሎ በነበሩት የትምህርት ዓመታት ገሚሱን የቀን ገሚሱን የማታ እያለ 12ኛ ክፍልን ለማጠናቀቀ በቃ። አጠናቆም ወደ ዩኒቨርሲቲ በመግባት ገና የ1ኛ ዓመት ተማሪ ሳለ የፖለቲካው እሳት እየነደደና ነበልባሉ እየተፋፋመ ሲመጣ በነበረው የኢህአፓ እንቅስቃሴ ትምህርቱን አቋርጦ ለመውጣት ተገደደ። ከመጽሐፍት ሻጭነት ወጥቶ እንደሄደውም ተመልሶ ወደ መጽሐፍ ሻጭነቱ ገባ። ሥራውን እያዳበረም ብዙ ደንበኞችን አፈራ። ከእነዚህ ደንበኞቹም መካከል አንደኛው ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ነበር። አውግቸው በዚህ ሥራው ውስጥ እየጠለቀ ሲሄድ ከመሸጫው ስፍራው እንደተቀመጠ ከመሸጡ ይልቅ ማንበቡ እየገዘፈበት ሄደ። ቁጭ ብሎ እያነበበ ቀልቡን ስለሚሰውረው ገዢው ፊቱ ቆሞ ሂሳቡን ሲጠይቀው ከተመስጦው የተነሳ በደመነፍስ ውሰደው ይል እንደነበረ በወቅቱ የሚያውቁት ይናገራሉ። ምናልባት ለዚህም ይሆናል ከእርሱ ጋር በመጽሐፍ ሽያጭ የነበሩ ጓደኞቹ ሁሉ የኋላ የመጽሐፍ ቤት ባለቤቶች ሲሆኑ እርሱ ግን ብቻውን መቅረቱ...

አውግቸውና ስብሐት...ከተቀራረቡ በኋላ የጻፋቸውን ጽሁፎች እንዲያይለት ለስብሐት ይሰጠው ነበር። ጽሁፎቹን ሲያደንቅለት የነበረው ስብሐትም አውግቸው በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ በአርታኢነት እንዲቀጠር አደረገው። በኩራዝ የነበረው ቆይታ ጥሩም ሆነ መጥፎ ለማለት ራሱ አውግቸውም የሚቸገርበት ይመስለኛል። እዚያ ቦታ ላይ ሁለት ጽንፍ የያዙ ነገሮች ወደ ሕይወቱ እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል። የመጀመሪያው ነገር የአርትኦት ሥራው ለደራሲነቱ የሚሆነውን ትልቅ ዕውቀትና አቅም ሸምቶበታል። በሌላ በኩል ደግሞ ፋታ አልባ ያደረገው ሥራው በአዕምሮ ህመም እንዲያዝ አድርጎታል። "እኔ የታመምኩት ኩራዝ



አውግቸው ተረፈ

> **ግንፍል ያደረገው ምን እንደሆነ ባይታወቅም አውግቸው ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ትግል ካልገጠምኩ ሲል ቤተ መንግሥት ድረስ ሄደ**

አሳታሚ ድርጅት ስሠራ ከጧት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ያለማቋረጥ አነብ ስለነበርም ነው" ብሎ ነበር ሲጠየቅ።

አውግቸው በደራሲነቱ የጻፈው እና ያስነበበው ቁጥር ፈጽሞ የሚመጣጠኑ አይደሉም። ቀን ከሌት እያነበበና እየጻፈ ውሎ ቢያድርም ለመጽሐፍነት አሊያም በሌላ አጋጣሚ ከአንባቢ የደረሱት ግን በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። ይጽፋል... ደግሞም ይጽፋል... ግን እንዴትና ምን ሆነው ከወዴትስ ገቡ? አይታወቅም። ምናልባት ከእርሱና ከእግዜሩ በስተቀር... በአንድ ወቅት ስብሐት ገ/እግዚአብሔር አውግቸው ይሰጠው ስለነበሩት ጽሁፎቹ ሲያነሳ ካላቸው ነገሮች ውስጥ እንዲህ የሚል ነበረበት፤ "አንድ ጊዜ ርዕስ የሌለው ረዥም ልቦለድ ደርሶ አንብቤው ከመጠን በላይ ተገርሜበት በኋላ ግን ጉድጓድ ውስጥ ጣለው" የሚል ነበር። አውግቸው ምን ተሰምቶት ይህን እንዳደረገ ግን የሚያውቅ አልነበረም። አብዛኛው ሥራዎቹም እንዲህና በመሳሰሉ ምክንያቶች ከማይታዩበት ቤርሙዳ ሰምጠዋል።

አውግቸውን በቅርበት ከሚያውቁት መሃከል አንደኛው ደራሲ አበረ አዳሙ ነው። በአንድ ወቅትም ከቢቢሲ ጋር ባደረገው ቆይታ ስለ አውግቸው ብዙ ነገሮችን አንስቶ ነበር። "ከአውግቸው ሥራዎች ወይ አዲስ አበባን የሚያክል የለም። የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክም የራሱ የአውግቸው ታሪክ ነው" ብሎ ያምናል። ብዙ ደራሲያን ስለ አውግቸው ጭምትነት በማንሳት ብዙ ማውራትም ሆነ ከሰዎች ጋር ጊዜ ማሳለፍን የሚመቸው ዓይነት አነበረም። ከዚያ ይልቅ ለብቻው ቁጭ ብሎ በጥልቀት ማሰብና ከራሱ ጋር ማውጋትን የሚመርጥ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ ቆራጥና በቃሉ ሕገ ደንብ የሚመራ፣ ያለውንና ያሰበውን ነገር ከመከወን ወደኋላ የማይል ሰው ነው። በ1987ዓ.ም አካባቢም የሆነው እንዲህ ነበር፤ አውግቸው በዚህም ዓመት ማንበብ ያለብኝ መዝገበ ቃላትን ነው ሲል እንደቀልድ ተናገረ። እንዳለውም ቃሉን ጠብቆ በዚያ ዓመት መዝገበ ቃላትን ብቻ ሲያነብ ከረመ። አውግቸው እንዲህ ያለው አስገራሚም ሰው ነበር። "ጎሩይ መጽሐፍትን እየሸጠ በነበረበት ወቅት ጽሁፎቹ በስብሐት በኩል በመጽሔቶች ላይ ይታተሙ ነበር። ታዲያ ጓደኞቹ አንተን ብሎ ደራሲ ብለው እንዳይዘባበቱበት ስለፈራ የሚጽፋቸውን አጫጭር ልቦለዶች በብዕር ስሙ ነበር የሚያወጣው" ሲል ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ተናግሯል። አውግቸው የብዕር ስሞቹ ብዙ ናቸው በማለትም ብዙዎች የማያውቁት "አዳነ ቸኮል" የተሰኘው የብዕር ስምም የእርሱ መሆኑን ይገልጻል። አውግቸውን በአርታኢነት ወደ ኩራዝ የወሰደው ስብሐት ነው የሚሉ ቢኖሩም እንዳለጌታ ግን ዳኛቸው ወርቁ ነው ይላል።

አስደምሞ አወዛጋቢው...ዝምተኛው አውግቸው አንዳንድ ጊዜ ድንገት እንደ መድፍ እየተተኮሰ በአስገራሚነቱ ላይ አወዛጋቢነትንም ያክልበታል። በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የሆነውም እንዲህ ነበር...ለዚህ የነሸጠው አሊያም ግንፍል ያደረገው ምን እንደሆነ ባይታወቅም አውግቸው ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ትግል ካልገጠምኩ ሲል ቤተ መንግሥት ድረስ ሄደ። በሩ ጋር ሲደርስ ደምስሩን ገትሮ ወደ ጠባቂዎቹ እያፈጠጠ "ኮሎኔል መንግስቱን ጥሩልኝ!" አለ። በሁኔታው የተገረሙት ጠባቂዎችም "እኮ ለምን?" ይሉታል በግራ መጋባት። "ትግል ልገጥመው እፈልጋለሁ" በማለት ቀጠለላቸው "እኔን ትግል ገጥሞ መጣል ሳይችል እንዴት ነው ሀገር ሊገዛ የሚችለው?" ሲል አምባረቀ። ይኼኔ ወታደሮች አፈፍ አድርገው ሰፈሩበት። ደህና አድርገው ከቀጠቀጡት በኋላ ወደ እስር ቤት ወረወሩት። ቀላል ለማይባል ጊዜም በእስር ሰነበተ።

ደራሲው ሞትን ወደ ሕይወት የለወጠ ጀግና ነው። በ1970ዎቹ አጋማሽ በአዕምሮ ህመም በአማኑኤል ሆስፒታል ውስጥ አሳልፏል። ለህመሙ መንስኤ ቀደም ሲል በአርትኦት ሥራው ከነበረበት ጫና ባሻገር በኋላም በብቸኝነት በሩን ዘግቶ ሲያነብ የነበረባቸው ጊዜያትም ጭምር ናቸው። ሃሳብና ጭንቀት እያበዛ ድባቴው ሲወቃው ከርሟል። ተደማምሮም ራሱን አጣው። ባጣው ራሱ ውስጥም ለማንም የማይገኘውን ነገር አገኘ። ያገኘውም "እብዱ" የተሰኘውን መጽሐፉን ነበር። ከሥራዎቹ ሁሉ ወጣ ያለና እጅግ አነጋጋሪም ነው። በዚህ ሁኔታ ፈጽሞ ማንም ሰው ይጽፈዋል ተብሎ የማይታሰብ ነበር። እብድ ጨርቁን ይጥላል እንጂ እብደቱን ጽፎ ያስነብባል ብሎ መጠበቅ እንዴትስ ተብሎ...ግን እርሱ አደረገው። በታሪክ እንዲህ እንደ አውግቸው በአዕምሮ መታወክ ውስጥ ሆኖ መጽሐፍ ለመጻፍ የቻለም ባለመኖሩ በዚህም የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም። ይህን መጽሐፍ ለየት የሚያደርገው በአዕምሮ ህመም ውስጥ ሆኖ ስለጻፈው ብቻ ሳይሆን በይዘቱም በሥነ አዕምሮ የህክምና ዘርፍ ውስጥ ለምርምርና ለማስተማሪያነት የመሆን አቅም እንዳለው ብዙ ዶክተሮች ምስክርነታቸውን ሰጥተውበታል። ለዚህ ለሠራው ጀብዱም በአማኑኤል ሆስፒታል ውስጥ ከሚገኙ ክፍሎች አንዱን በስሙ ሰይመውለታል። አውግቸው ከተበረከቱለት ሽልማቶች መካከል የ2008ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት አንዱ ነበር።

የዝነኛው መጨረሻ...ሁሉን አልፎ ከሁሉም ለማለፍ ሲቃረብ ግራጫ የሕይወት ጥላ አጠላበት። ያቺ መነሻው የነበረችው መርካቶ ለመጨረሻው ጥቂት እስኪቀረው መኖሪያው ነበረች። ከሰዎች ጋር ለጨዋታም ሆነ ወጣ ብሎ ከቤቱ ለመራቅ አልተቻለውም። በዚያ ላይ ደግሞ ምኑም ባልገባው የአንገት በሽታ ለመዟዟር ተስኖት በስቃይ አሳልፏል። ትዳር ይዞ ሁለት ልጆችንም ለማፍራት ችሏል። መጨረሻውም ይኼው ነው...ሰኔ ከሰኞው ተጋጠመና ሰኔ 10 ቀን 2011ዓ.ም አውግቸው ጎሩይና ንጉሤንም ይዞ አረፈ። ሞተ። ጻፈ አስደመመ። ጻፈ ተደነቀ። ኖረ አወዛገበ። ሁሉንም ያውቅበታል። ሁሉንም ይችልበታል።

# ዓለም አቀፍ

## የሩስያ የፀጥታ ኃይሎች በእስር ቤት የታገቱ ሠራተኞችን አስለቀቁ

የሩስያ ብሔራዊ ዘብ ታጋቾችን ለማስለቀቅ እና እስር ቤቱን ለመቆጣጠር ባከናወነው ሥራ የታገቱ ሠራተኞችን እንደአስለቀቁ አስታውቋል፡፡ አራቱም አጋቾች በአልሞ ተኳሾች (ስናይፐርስ) መገደላቸው ነው የተነገረው፡፡

በሩሲያ ወጣ ብሎ በሚገኝ እስር ቤት በርካታ እስረኞች ባስነሱት አመፅ እና በፈፀሙት እገታ አራት የእስር ቤቱ ሠራተኞች መገደላቸውን የፌደራል ባለሥልጣናት አስታወቁ። በደቡብ ምዕራብ ቮልጎግራድ ክልል በሚገኘው አይኬ-19 ሱሮቪኪኖ በተባለው እስር ቤት 'የእስላማዊው መንግሥት ታጣቂዎች ነን' ያሉ ስለት የያዙ እስረኞች ሕንጻውን መቆጣጠራቸውን ከገለጹ በኋላ የፌዴራል ልዩ ኃይል በሕንጻው ላይ ኦፕሬሽን አካሂዷል።

ባለሥልጣናት እንዳሉት ልዩ ኃይሉ የሠራው ኦፕሬሽን የተወሰኑ ታጋቾችን ነፃ ያወጣ ሲሆን ጥቃት አድራሾቹም እንዲለዩ አድርጓል። ሆኖም በኋላ ላይ አራት የእስር ቤቱ ሠራተኞች መሞታቸው ተረጋግጧል። ያልተረጋገጠ እና በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተጋራ ምስልም በአመፁ ወቅት አንድ በእጁ ስለት የያዘ እስረኛ በደም ከተለወሰ የእስር ቤት ጠባቂ በላይ ቆሞ አሳይቷል።

የሩሲያ ሮስግቫርዲያ ብሔራዊ ዘብ በበኩሉ በነፍስ አድን ኦፕሬሽኑ ወቅት አልሞ ተኳሾች አራት ጥቃት አድራሾች ላይ ተኩሰዋል ብሏል። በብሔራዊ ዘቡ የቴሌግራም ገፅ ላይ በተጋራ ምሥል ላይም የታጠቁ ወታደሮች በእስር ቤቱ ውስጥ ሲደርሱ አሳይተዋል። የሩሲያ የፌዴራል ማረሚያ ቤት አገልግሎት በሰጠው መግለጫ እንዳለው ጥቃቱ የተጀመረው በሥነ ምግባር ኮሚሽን ስብሰባ ወቅት ነው።

ጥቃት አድራሾቹ የእስር ቤቱን ጠባቂዎች ገድለው በርካታ የእስር ቤቱን ሠራተኞች አቁስለዋል ተብሏል።




ከዚህም በተጨማሪ ስምንት የእስር ቤቱ ሠራተኞች እና አራት ፍርደኞች ታግተው መወሰዳቸውን የማረሚያ ቤቱ አገልግሎቱ ገልጿል። ታግተው ከተወሰዱት መካከል የእስር ቤቱ ዋና ዳሬክተር እና ምክትል ዳሬክተሩ እንደሚገኙበት አንዳንድ የሩሲያ ሚዲያ ዘገባዎች አመልክተዋል።

"ወንጀለኞቹ በአራት ሠራተኞች ላይ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት ያደረሱ ሲሆን ሦስቱ ሞተዋል። ሌሎች ጥቃቱን የተጋፈጡ አራት ሠራተኞች ደግሞ ሆስፒታል ገብተው፣ አንዱ በሆስፒታል ሕይወቱ አልፏል።" ብሏል።

የማረሚያ ቤት አገልግሎቱ ጥቃት ፈፃሚዎቹ ሙሉውን የእስር ቤቱን ሕንጻ ተቆጣጥረው ነበር መባሉን አስተባብሏል። "ጥቃት አድራሾቹ ታጋቾችን በሕንጻው በሚገኝ አንድ ክፍል ውስጥ ነው ያገቱት" ብሏል። እገታው ቀድሞ የታሰበበትና በሚገባ የታቀደ እንደነበር የሩሲያ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ታስ አንድ ሕግ አስፈፃሚ አካልን ጠቅሶ ዘግቧል።

መገኛና ብዙኃኑ ጥቃት ፈፃሚዎቹ የ28 ዓመቱ ራምዚዲን ቶሾቭ፣ የ23 ዓመቱ ኡሰታምጆን ናቭሩዚ፣ የ28 ዓመቱ ኖዚርጆን ቶሾቭ እና የ29 ዓመቱ ተሙር ኹሲኖቭ መሆናቸውን በስም ለይቷል። ሁሉም የኡዝቤኪስታን እና ታጃኪስታን ተወላጆች ናቸው ብሏል።

በጥቃት ፈፃሚዎቹ በተጋራ በሞባይል የተቀረፀ ምሥል ላይ ግለሰቦቹ የአይኤስ ታጣቂዎች መሆናቸውን ሲገልጹ ታይተዋል። በተንቀሳቃሽ ምሥሉ ላይ ግለሰቦቹ ጥቃቱን የፈፀሙት በሙስሊሞች ላይ የሚደርሰውን ግፍ ለመበቀል በማሰብ እንደሆነም ተናግረዋል። ከዚህም በተጨማሪ በተንቀሳቃሽ ምሥሉ ላይ ባለሥልጣናቱ በደም ተነክረው ወድቀው ያሳያል። በሌላ ቪዲዮ ላይ ደግሞ ጥቃት ፈፃሚዎቹ በእስር ቤቱ ግቢ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ታይተዋል።

የቮልጎግራድ ግዛት ገዥ አንድሬ ቦቻሮቭ ቀደም ብለው በታጋቾች መወሰዳቸው በሠላማዊ ነዋሪዎች ላይ ምንም ስጋት እንዳልፈጠረ ተናግረዋል። ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲንም በበይነ መረብ አማካኝነት በተካሄደ የፀጥታ ኃላፊዎች ስብሰባ ላይ ሲካፈሉ የታዩ ሲሆን ስለሁኔታው እንደተነገራቸው ተገልጿል። በተያዘው የበጋ ወቅት በቮልጎግራድ እገታ ሲፈፀም ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።

ከዚህ ቀደም በጎረቤቷ ሮስቶቭ ክልል ከእስላማዊ መንግሥት ቡድኑ ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ስድስት እስረኞች ሁለት የእስር ቤቱን ጠበቂዎች አግተው ወስደው ነበር። ከአጋቾቹ መካከል አምስቱ የተገደሉ ሲሆን አንደኛው ጥቃቱን ተከትሎ የ20 ዓመታት እስር ተፈርዶበታል። አቃቤያነ ሕጎችም ከእገታው ጋር በተያያዘ የክስ ፋይል መክፈታቸውን ተናግረዋል።

አይኬ-19 ሱሮቪኪኖ ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግለት የወንጀለኞች እስር ቤት ሲሆን 1 ሺህ 200 የሚጠጉ እስረኞች እንደሚገኙበት ይገመታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

አዲስ ዘመን | እሁድ ነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም

# ነፃ ሃሳብ

# አትሌቲክሳችንን ከህመሙ ማን ይፈውሰው ይሆን?

**ተሾመ ቀዲዳ (ከበሪሳ ጋዜጣ)**

ኢትዮጵያ በዓለም ከምትታወቅባቸው መካከል አንዱና ግንባር ቀደሙ የአትሌቲክስ ስፖርት ነው። ጀግኖች አትሌቶች አበበ ቢቂላና ማሞ ወልዴ በሮም፣ በቶኪዮና ሜክሲኮ ኦሎምፒኮች በማራቶን በተከታታይ በማሸነፋቸው እስከ አሁን የኢትዮጵያ ስም በኦሎምፒክ መዝገብ በክብር በወርቅ ተጽፎ ይገኛል።

እንዲሁም በሞስኮ፣ በባርሴሎና፣ በአትላንታ፣ በሲድኒ በአቴንስ፣ በቤጂንግ፣ በለንደን፣ በሪዮና በቶኪዮ አደባባዮች ስመጥር አትሌቶች በሁለቱም ፆታዎች ድል ማድረጋቸው የአበበና ማሞ ወልዴን ጀግንነት ደጋግሞ አሳይቶናል። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከበለጸጉት ሀገራት ሰንደቅ ዓላማ በላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብና መዝሙሯም ከዳር እስከ ዳር የዓለም ሕዝብ ጆሮ እንዲገባ አድርገዋል። ብሔራዊ መዝሙሯም ሲዘመርና ሰንደቅዋ ሲውለበለብ ባለታሪኮቹ አትሌቶች በሀገር ፍቅር ስሜት አንብተዋል።

በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን የድሉ ተካፋይ በመሆን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በሆታና በጭፈራ ደስታቸውን በአደባባይ ገልፀዋል። የድሉ ባለቤት የሆኑት አትሌቶቻችን፣ አሰልጣኞችን የቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ወደ ሀገራቸው በድል ሲመለሱ ወገን በሙሉ ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ እስከ ይፋዊ የአቀባበል ሥነ ሥርዓት የሚካሄድባቸው ቤተመንግሥትና ስታዲየም አጅበዋቸዋል።

መንግሥታትም በየዘመናቱ በድል ለሚመለሱ ጀግኖች አትሌቶቻችን ሹመትና ሽልማት አበርክቷል። ሕዝቡም በየክልሉ ጥሪ በማድረግ እነዚህን ከአብራኩ የወጡትን ጀግኖች ልጆቹን በክብር ተቀብሎ የተለያዩ ሽልማቶችን አበርክቶላቸዋል። መንግሥታት ከሹመትና ሽልማት ባሻገር የእነዚህ ጀግኖች ስምና የታሪክ ገድል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በስማቸው አደባባይ፣ ስታዲየም፣ አካዳሚዎች፣ ሆስፒታል መንገድና ት/ቤት እንዲሰየም አድርገዋል።

እነዚህ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በማሸነፍ የሀገራችንን ስም በክብር ያስጠሩት አትሌቶቻችን በላባቸውና በደማቸው ያገኙትን ሀብት ዛሬ በሀገራቸው ሥራ ላይ በማዋል ከስፖርቱ ባሻገር በልማት (ኢንቨስትመንት) መስክ በመሰማራት ሀገራቸውን፣ ሕዝባቸውንና መንግሥታቸውን በማገዝ እጥፍ ድርብ ውለታ በመክፈል ላይ ይገኛሉ። ከዚህም ባለፈ በይፋ ባይታወቅም እነሱን የሚተኩ አትሌቶች በያሉበት ሥፍራ በገንዘብ፣ ከቁሳቁስና በሞራል ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በከፈቱት የሥራ መስክም በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን የሥራ ዕድል በመክፈት ተሰማርቶ ከራሳቸው አልፎ ለቤተሰቦቻቸው ብሎ ለሀገር ጭምር እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የዚህ የአትሌቲክስ ስፖርት አካል የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላ አፍሪካ፣ ብሎ በዓለም እንዲታወቅ በር የከፈተውና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው የዓለማችን ምርጥ አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ በትውልድ ዘንድ ዘለዓለማዊ ስሙን ተክሎ የሚያልፍ ድንቅ ታሪክና ተግባር እየፈጸመ ይገኛል። ይህ ታላቅ ሰው የዚሁ ባለድል አትሌቲክሳችን ውጤት ነው።

የኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ስፖርት ታሪክ እስከ አሁን እንደ ኦሎምፒክ ችቦ የቅብብሎሽና የመተካካት ወቅቶች ነበሩት። የእነ ዋሚ ቢራቱ፣ ባሻዬ ፈለቀ፣ አበበ በቂላ፣ አበበ ዋቅጅራ ዘመን ለእነ ማሞ ወልዴ ዘመን ተሸጋገረ። ከዚያ ወደ እነ ምሩፅ ይፍጠር የአረንጓዴ ጎርፎቹ መሐመድ ከድር፣ ብርሃኑ ግርማ፣ እሸቱ ቱራ፣ ግርማ ወልደ ሃና፣ ከበደ ባልቻ ደረጀ ነዲና ቶለሳ ቆቱ ተላለፈ። እንዲሁም መገርሣ ቱሉ ትዕዛዙ ውብሸት፣ ተክሌ ፈንቲሳ፣ ገብሬ ጉርሙ፣ ሁንዴ ጦሬ የመሳሰሉት እያለ ቀጠለ።

ይህ ወርቃማው ዘመን በዚህ ሳያበቃ እነ አበበ መኮንን ወደ ጀቡልቲ፣ ሐጂ ቡልቡላ፣ በቀለ ደበሌ፣ እነ ወልደ ሥላሴ ሚልኬሳ፣ የኃይሌ ገ/ሥላሴ ታላቅ ወንድም ተክዬ ገብረ ሥላሴ መሰሎቹ ተላለፈ።

ከዚያ ወደ ጀግኖቹ የዓለምና ኦሎምፒክ ባለ ድሉ ፊጣ ባይሳ፣ ጠና ነገሪ፣ ወርቁ በቂላ፣ ወንድማማቾቹ ሃብቴና ተስፋዬ ጅፋር፣ አሰፋ መዝገቡና ወንድሙ አየለ መዝገቡ፣ ሚሊዮን ወልዴ፣ ሐዱሽ አበበና አብርሃም አሰፋ ስምረቱ ዓለማየሁና ሌሎች የወቅቱ ጀግኖች ቀጠለ።

ከዚያም በተሳተፈባቸው የኦሎምፒክና የዓለም ሻምፒዮና ሪከርድ ጭምር በመስበር ወደሚታውቀው ጀግናው ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ የማራቶኑ ጀግና ገዛኸኝ አበራና ተስፋዮ ቶላ፣ ማርቆስ ገነቴ፣ ግርማ ቶላና ኃይሉ መኮንን እያለ ከዚህ ትውልድ በትረ ስልጣኑን የድል ባንዲራ የተቀበለው የኦሎምፒክ፣ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናና የሀገር አቋራጭ ንጉስ ቀነኒሳ በቀለና ታሪኩ በቀለ ፣ ስለሺ ስህንና እነ ገብረ እግዚአብሔር ገብረማሪያም አሊ አብዶሽ፣ አብዮት አባተ፣ ፀጋዬ ከበደ፣ ኢብራሂም ጀይላን አርበኛው የሪዮ ኦሎምፒክ ጀግና ፈይሳ ሌሊሳ እያለ የዛሬ ትውልድ ደርሷል።

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ታሪክ በወንዶች ብቻ ሳትወሰን ከሀገር አልፎ ለአፍሪካም ጭምር ጀግንነት ሰርተው በክብር ያስጠሩን ድንቅ ሴት የአትሌቲክስ ጀግኖች የፈጠረች ሀገር መሆንዋን በመላው ዓለም የስፖርት መድረክ አስመስክራለች። የሞስኮ ኦሎምፒክ ፈር ቀዳጆቹና ተሳታፊዎቹ ፋንታዬ ሲራጅና ኢትዮጵያ ገብረ እግዚአብሔር፣ እነ ፅጌ ገብረመስቀል፣ ጌጤነሽ ኡርጌ፣ ሉቺያ ይስሀቅ፣ ዘውዴ ኃይለማርያም፣ አየለች ወርቁ፣ ቁጥሬ ዱለቻን የመሳሰሉትን አፍርታለች። ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ ለአፍሪካ በኦሎምፒክ በ10 ሺ የወርቅ ሜዳሊያ ያመጣችውን የባርሴሎና ኦሎምፒክ ጀግኒት ደራርቱ ቱሉን ያፈራች ሀገር ናት።

ደራርቱ ቱሉ የኢትዮጵያ ሴት ጀግኖች አትሌቶች እነ ጌጤ ዋሚ፣ ብርሃኔ አደሬ፣ የኦሎምፒክ ማራቶን ጀግናዋ ፋጡማ ሮባ፣ ቲኪ ገላናን፣ እልፍነሽ ዓለሙ፣ መስታወት ቱፋ፣ መሪማ ደንቦባና መሬማ ሐሺም፣ ገለቴ ቡርቃን የመሳሰሉትን ከኋላዋ አሰልፋ በየውድድሩ ሜዳዎች ብቅ ስትል በፍቅርና በደስታ ተመልካች ከዳር እስከ ዳር ስታዲየሙን በጭብጨባና በፉጨት ያናውጣል።

አበባዋ ደራርቱ በአትሌቲክስ ስፖርት ፈር ቀዳጅነት ዛሬ መላውን ዓለም በማራቶን በአሥር ሺ፣ በአምስት ሺ፣ በሶስት ሺ መሰናክል፣ በ1500 በመካከለኛ ርቀትና በአጭር ርቀቶች ጭምር የተቆጣጠሩ አፍሪካውያን ሴት ጀግኖች እንደ አሸን መፍለቅ እንዲችሉ የመድረኩ መሪ ተዋናይ ሆና ለዘላለም ስምዋ በታሪክ በክብር እንዲነሳ አድርጋለች።

የኢትዮጵያ ስፖርት አባት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ የአትሌቲክስ ስፖርት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም። አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ንጉሴ ሮባን በአትሌቲክስ ስፖርት የፈጠሩ ታላቅ ሰው ናቸው። አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባ ደግሞ ዶ/ር ወልደመስቀል ኮስትሬ፣ ዶ/ር ይልማ በርታን፣ ሻምበል ቶሎሳ ቆቱን አበቁ። ከዚያ የብሔራዊ ክለቦች አሰልጣኞች እነ ሻምበል እሸቱ ቱራ፣ መሐመድ ከድር፣ ዮሐንስ መሐመድ፣ ብርሃኑ ግርማ፣ ግርማ ወ/ሃና፣ ካሱ ዓለማየሁ ትዕዛዙ ውብሸት በዚህ ውስጥ ደግ የተለያዩ አትሌቶችን በማደራጀት ያሰለጥኑ የነበሩ ታላቁ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፈር ቀዳጅ ዋሚ ቢራቱን ሳንረሳ እነዚህ እንከን የማይወጣላቸው አሰልጣኞች ተገኙ።

እነሱም ሀገርን የበለጠ ለኩራት ያበቁ ድንቅ አትሌቶች ከማብቃት አልፎ ወጣት አትሌቶችን ከሥር በመተካት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው። ለአብነት የአትላንታ፣ ሲዲኒ፣ አቴንስ፣ ቤጂንግ፣ ለንደን ኦሊምፒክ እና የዓለም አሌቲክስ ሻምፒዮና በተለይም በሔልሲንኪና ኤድመንተን ሻምፒዮናዎች የዶ/ር ወልደመስቀልና ኮስትሬና የሻምበል ቶሎሳ ቆቱ ውጤት ቢሆንም የክለብ አሰልጣኞች ሚናና አጋርነትም በቀላሉ የሚታይ አልነበረም።

ጀግኖቹ የኦሊምፒክ፣ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናና ሀገር አቋራጭ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚዎች እነ ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ፋጡማ ሮባ፣ ቀነኒሳና ጥሩዬ የመሳሰሉ ውለታ ሳይረሳ ወደ የዛሬዎቹ ታሪክ ሠሪዎች ታምራት ቶላ፣ ትዕግሥት አሰፋ፣ በሪሁ አረጋዊና ሲንቦ ዓለማየሁ ለሀገር የሰሩት ውለታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ተሳትፎ ከ1956 የፈረንጆች አቆጣጠር የጀመረ ነበር። ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ተሳትፎዋ እንደተባለው በተሳትፎ ብቻ ነበር የተመለሰችው። ወርቅ፣ ብርም፣ ነሐስም አልተገኘም። ነገር ግን ከሮም እስከ ፓሪስ በ14 ኦሎምፒኮች አንድም ጊዜ ከሜዳሊያ ውጪ ሆና አታውቅም፣ 24 ወርቅ፣ 15 ብር እና 23 ነሐስ በድምሩ 62 ሜዳሊያ አግኝታለች።

እውነታው ይሄ ቢሆንም ታዲያ ምን ያደርጋል ዛሬ ላይ ሆነን ስንመለከተው የመተካካቱ ጉዳይ ያበቃ ይመስላል። ከአበበ በቂላ ጀምሮ እስከ ታምራት ቶላ ያለው ትውልድ አደራ ጠብቆ እዚህ አድርሶናል። ከንጉሴ ሮባ ጀምሮ ዘመናዊ ስልጠናን በሚገባ ጠብቆ እስከ ወልደመስቀል ኮስትሬና ቶለሳ ቆቱ አድርሶናል። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ማን ይሆን የአደራውን ሰንደቅ ዓላማ የሚረከበው የሚለው ጥያቄ የብዙ ኢትዮጵያውያን ስፖርት አፍቃሪዎች ጥያቄ እየሆነ መጥቷል።

ሰሞኑን 33ኛው የፓሪስ ኦሎምፒክ የባሰውኑ ገመናችንን ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል። ተተኪን የሚፈጥር አመራር ሳይሆን ስፖርቱን የሚያሽብር አመራር መፈጠሩን፣ ጠንካራ የአትሌቲክስ አሰልጣኝ በተለይም የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ከመፍጠር የቤተሰብ አሰልጣኝ መፈጠሩ፣ ለሀገርና ለወገን እንዲሁም ለውጤት የሚሮጥ አትሌት ከመፍጠር ይልቅ ገንዘብ አግኝቶ አሰልጣኞችን የሚያበለጽግ አትሌት መፈጠሩን አመላክቶን አልፏል።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ከሪዮ መልስ ውጤታችን አሽቆልቁሏል በማለት አፈርሳታ ወጥቶ አዲስ አመራር እንዲፈጠር ሲባል በተደረገው ጥያቄና ንቅናቄ የአዲሱን አመራር መምጣት ተቀብለው ከተደሰቱት አንዱ ነበርኩ። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ይነሳ የነበረው ጥያቄ በየዘመኑ የሚመረጡ የፌዴራሽን አመራሮች በስፖርት ውስጥ አላለፉም፣ ስለ አትሌቶች ድካምና ጉዳት በደንብ አያውቁም ወይም አልተረዱም በማለት በየጊዜው በአትሌቶች የሚነሱ እሮሮና ጥያቄ መልስ ያገኛል የሚል ተስፋን በመሰነቅ ነበር።

አዲሶቹ አመራሮች በተለይም በዓለም የአትሌቲክስ መድረክ ሀገርን ያኮሩ፣ በሕዝባቸው፣ በመንግሥትና ደጋፊዎቻቸው ዘንድ የተከበሩና ተቀባይነት ያላቸው እነ ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ገብረ እግዚአብሔር ገብረማርያም፣ ገዛኸኝ አበራ ማርቆስ ገነቲ፣ መሰለች መልካሙ ታላቁ አሰልጣኝ ሻምበል ቶሎሳ ቆቱ፣ አበበ መኮንን በኋላ ረ/ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ከአትሌቶች መሃል የወጡና የአትሌትክሱን ችግር ቀምሰው ያለፉ፣ ለአትሌቱ ዕድገት የሚጥሩና ከፍ የሚያደርጉ አውቀው የሚያሳውቁ መስሎኝም ነበር።

ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነና ከውጤቱ ይልቅ ንትርክና ጭቅጭቅ፣ ከጽ/ቤቱ ወደ አደባባይ በመውጣት ገመናችንን አጋለጡ። በሪዮ ኦሎምፒክ የታየው ድክመታችን ምንም ሳይታረም በቶኪዮ ተደገመ፣ ይባስ ብሎ በፓሪስ ቀደም ሲል በምንታወቅባቸው ውድድሮች በተለይም 10 ሺ እና 5 ሺ ሜትር ሜዳልያ ከእጃችን ወጣ።

> **ዛሬ የኛን ውጤት ነጥቀውን እኛ ደግሞ በተራችን ቁጭ ብለን እያጨበጨብን እንድናደንቃቸው ተደርገናል። ኢትዮጵያ የምትታወቀው በአትሌቲክስና በቡና ነው ይባል ነበር**

ትናንትና እኛ አፍሪካን በምናስተዋውቅበትና በምንታወቅበት 10 ሺ ሜትር ውጤታችንን ለሌሎች ሀገሮች አሳልፈን እንድንሰጥ ተገደናል። ትናንትና የኢትዮጵያ ጀግኖች በድል አድራጊነት በሜዳሊያ ሲታጀቡ በአድናቆት እያጨበጨቡ የሚደግፉን ሀገሮች፣ ዛሬ የኛን ውጤት ነጥቀውን እኛ ደግሞ በተራችን ቁጭ ብለን እያጨበጨብን እንድናደንቃቸው ተደርገናል። ኢትዮጵያ የምትታወቀው በአትሌቲክስና በቡና ነው ይባል ነበር። ዛሬ ግን አትሌቲክሱን ለሌላ ሀገር አሳልፈን ሰጥተን ቁዘማ ታቅፈን ቀርተናል የሚሉ ወገኖች ብዙዎች ሆነዋል።

ስለሆነም አንድ ዓይን ያለው በአፈር አይጫወትም እንደሚባለው መኩሪያችን የሆነው አትሌቲክሳችን ይበልጥ አሽቆልቁሎ የሀገራችን ዝናና ኩራት የበለጠ ዝቅ እንዳይል የሚመለከተን ሁሉ በጋራ የምንሠራበት ጊዜ አሁን ነው እላለሁ!

# ስፖርት



## ‹‹የተሰጠንን በረከት ማወቅ ካልቻልን መርገምት ነው የሚሆንብን››

- አቶ ደቻሳ ጅሩ

ብርሃን ፈይሳ

በዘመናዊው ዓለም በተለይም ባደጉት ሀገራት የስፖርት ሥልጠናዎች ሳይንሳዊ መንገድን ተከትለውና በቴክኖሎጂ ታግዘው እንደሚሰጡ ይታወቃል። በአንድ የስፖርት ቡድን ውስጥም ከአትሌቶችና ከአሠልጣኞች ባሻገር የጤና፣ የሥነ ምግብ፣ ሥነልቦና፣ የውድድር ትንተና ወዘተ ሙያተኞችን ማሰባጠር የተለመደ አሠራር ነው። ከአተነፋፈስ ሥርዓት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው የአትሌቲክስ ስፖርት ደግሞ የሥልጠና እና የውድድር ሁኔታን ከአየር ንብረቱ ጋር እንዲመጣጠን በማድረግ ረገድ የሚሠሩ ባለሙያዎችም የአሠልጣኞች ቡድን አካል ናቸው። አትሌቶች ምቹ በሆነ የአየር ሁኔታ ሥልጠናቸውን ከመከታተል ባለፈ በቤተሙከራ ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን አየር እየተነፈሱ እንዲለማመዱ በማድረግም ለውጤት ያበቋቸዋል።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ተሞክሮ ኋላ ቀር የሚባል ሲሆን፤ ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ተመሳሳይ ሊባል ከሚችል ተለምዷዊ የሥልጠና ስልት ሊላቀቅ አልቻለም። በውድድሮች ላይ ውጤታማ አለመሆን ዛሬም ድረስ የአየር ሁኔታ ሰበብ እንደሆነ ዘልቋል። በዚህም ምክንያት ተፎካካሪ አትሌቶች የታወቀውን የኢትዮጵያውያን መንገድ ጠንቅቀው በማወቅ የበላይነቱን በመረከብ ላይ ይገኛሉ። ከዘመናዊው ዓለም ጋር ሊያራምዱ የሚችሉ ሳይንሳዊ አማራጮችን ይዘው የሚቀርቡትንም የሚቀበል አለመሆኑን የዛሬው ቃለምልልስ እንግዳችን ተሞክሮ ማሳያ ነው።

በተቀናጀ የእርሻና ደን ጥምር ጥናት ዘርፍ ለግማሽ ምዕተ ዓመት በተመራማሪነት ያሳለፉት አቶ ደቻሳ ጅሩ፤ ከሃገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባለፈ በጣሊያን እና አውስትራሊያ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ሙያቸው እህል ማምረትን፣ ከብት ማርባትን እና ዛፍ ማልማትን ያካተተ ሲሆን፤ የሰው ልጅ ምድቡ ከእንስሳት ወገን በመሆኑ ከአየር እና ሥነምሕዳር ምቹነት ጋር በተያያዘ በርካታ ጥናቶችን ማከናወን ችለዋል። በልጅነታቸው ሩጫን የሚወዱ ቢሆንም ገፍተው መሄድ አልቻሉም፣ ነገር ግን በሙያቸው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርትን ከአየር ንብረት እና ሥነምሕዳር አንጻር በምን መልክ ቢሠራበት ውጤታማ መሆን ያስችላል በሚለው ላይ ምርምር አድርገዋል። በተለያዩ ጋዜጦች ሙያዊ ምክረ ሃሳቦችን በማሳተምም ለአትሌቲክሱ ይበጃል የሚሉትን ከመጠቆም ወደኋላ ብለው አያውቁም።

**አዲስ ዘመን፡- አትሌቲክስን ከተቀናጀ የእርሻና ደን ጥምር ጥናት ዘርፍ ጋር በምን መልኩ ማያያዝ ይቻላል?**

**አቶ ደቻሳ፡-** በኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ መረጃ ግርድፍ በመሆኑ የአየር ተስማሚነትን በግልጽ ያንጸባርቃል ለማለት አያስችልም። የአየር ሁኔታ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ እርጥበት፣ ንፋስ፣ ደረቅ፣ ... እየተባለ የሚለይ ሲሆን ይህንን በውል ለይቶ አለማወቅ አትሌቲክስን ጨምሮ በየትኛውም ዘርፍ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል። በርካታ ጥናቶች በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ያለው የአየር ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለይተው ስለሚያስቀምጡ ይህንን መለየትና መከታተል አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይሁንና በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችን በማሳተፍ ትክክለኛውን መረጃ በማግኘት ጥራት ያለው ሥራ ከመተግበር አንጻር ክፍተቶች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውጤታማነት ምክንያት የአየር ንብረቷና መልክዓምድሯ መሆኑ ይነገራል። ይህ በባለሙያ ዓይን እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ደቻሳ፡-** በአፍሪካ 40 ከመቶ የሚሆነው ከፍተኛ ስፍራ መገኛው ኢትዮጵያ ነው። ይህም ቀዝቃዛ የሚባል የአየር ሁኔታ ሲያላብሰው ከአተነፋፈስ ጋር በተያያዘ የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በከፍታማ ስፍራዎች ላይ ኦክስጅን እየሳሳ ስለሚሄድ አተነፋፈሱ እንደልብ አይሆንም። ስለዚህም ሰውነታቸው የሚያመነጨው የሄሞግሎቢን እንዲሁም የብረት ክምችት መጠን ከፍተኛ ነው። እንደ ኃይሌ ገብረሥላሴ እና ቀነኒሳ በቀለን የመሰሉ ድንቅ አትሌቶች ደግሞ በተፈጥሮ ከተለመደው በእጥፍ የጨመረም ነው። በመሆኑም በከፍታ አካባቢ ያደጉ ሰዎች የትኛውንም የአየር ሁኔታ የመቋቋም አቅምን ያዳብራሉ። አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ረጅም ርቀት አትሌቶች ውጤታማ የመሆናቸው ምክንያትም በከፍተኛ ስፍራዎች ላይ ያደጉ በመሆናቸው የተቸራቸው በረከት ነው።

ለአብነት ያህል ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ውጤታማ የሆነችባቸው ከተሞች ከባሕር ጠለል በላይ ያላቸውን ከፍታ ብንመለከት፤ ሲድኒ 28 ሜትር፣ አቴንስ 23 ሜትር እንዲሁም ቤጂንግ ከ40-60 ሜትር ናቸው። ይህም ዝቅተኛ ቦታ መሆኑን ሲያሳይ፤ በዝቅተኛ ስፍራ ኦክስጅን እንደልብ መሆኑ ለአትሌቶቻችን ጠቅሟቸዋል። በመሆኑም አትሌቶችን ወደ ውድድሮች ከመላክ አስቀድሞ ከአየር ሁኔታ ጋር የተያያዘ መረጃ መመልከትና መለየት አስፈላጊ ነው። ሌላው ጉዳይ አመጋገብ ሁኔታ ነው፤ ‹‹አጃማ ብመገብ አሁን ማን ችሎኝ፤ ቀለቤ ገብስ ነው በሶ አደከመኝ›› እንደተባለው በከፍታማ አካባቢዎች የሚዘወተሩ ምግቦች በአትሌቶች ውጤታማነት ላይ የራሳቸው ዋጋ አላቸው። በመሆኑም የአካባቢውን ባሕል መሠረት በማድረግ በምርምር ተደግፈው መቅረብ አለባቸው። ስፖርቱ ላይ ያሉ ባለሙያዎችም ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በቂ ማብራሪያ እና ትንታኔ እንዲሰጧቸውም መጠየቅን መልመድ ይገባቸዋል። ከውጤት ጋር በተያያዘም በምን ምክንያት እንደተገኘ መገምገምና መከታተል ካልተቻለ ፉክክር በበዛበት በዚህ ዘመን ስኬታማ መሆን አይቻልም።

**አዲስ ዘመን፡- ከመልክዓ ምድርና የአየር ፀባይ አኳያ በሌሎች የስፖርት አይነቶችስ ኢትዮጵያን ውጤታማ ሲያደርግ የሚችል ምቹ ሁኔታ የለም?**

**አቶ ደቻሳ፡-** ከከፍታ ቦታዎች ወደታች ስንወርድ እንደ ዳሎል አይነቱን እጅግ ዝቅተኛ ስፍራ እናገኛለን። ከምድር ወገብ በጣም የራቁ ሃገራት የአየርና የመልክዓ ምድር ሁኔታው እጅግ እየተለየና ከባድ እየሆነ ይሄዳል። በዚህም ምክንያት ክረምታቸው እጅግ በጣም ቀዝቃዛና በበረዶ የተሸፈነ፤ በበጋ ደግሞ የሙቀት መጠኑ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል። በአንጻሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገራት ለሁሉም ምቹ የሆነና የተመጠነ የአየር እና የቦታ አቀማመጥ አላቸው። ይህም በስፖርቱ በርካታ አማራጮች እንዲኖረን የሚያስችል በመሆኑ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል። በአትሌቲክስም ከውድድር መልስ ውጤት ጠፋ በሚል የሚነሳ የጅምላ ምክንያትንም ያስቀራል። በመሆኑም ለ2028ቱ የሎስ አንጀለስ ኦሊምፒክ ከወዲሁ ይህንን ሁኔታ ለይቶ በቅንጅት ወደ ዝግጅት መግባት ያስፈልጋል። የተሰጠንን በረከት ማወቅ ካልቻልን መርገምት ነው የሚሆንብን።

**አዲስ ዘመን፡- በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች የኢትዮጵያ ውጤት ስለመቀነሱ ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ነገሮችን ምክንያት አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል?**

**አቶ ደቻሳ፡-** አትሌቶችን የምናሠለጥንበትን ስፍራ ለየትኛው ርቀት ይሠራል የሚለውን ለይተን አለማየታችን አንዱ ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ተሳትፎዋ ከፍተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘችው በሲድኒ መሆኑ ይታወቃል። በዚያ ውድድር ላይ ከተሳተፉ አትሌቶች ውስጥ ወርቅ ያስመዘገቡት ብዙም ልምድ የሌላቸው ወጣቶች እንዲሁም ከወሊድ መልስ በተወዳደረችው ደራርቱ ቱሉ ነው። ይህም የሚያረጋግጠው ለአትሌቶቹ ውጤታማነት የሲድኒ ምቹ የአየር ሁኔታ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ነው። በመሆኑም በምልመላ፣ በአካላዊ ቅርጽ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በሳይንሳዊ ሁኔታ ታግዞ በመለየት አተኩሮ መሥራት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በተገቢው አየር አለመዘጋጀት አንዱ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።


**አዲስ ዘመን፡- በአትሌቲክስ ውጤት ላይ ምን ዓይነት ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ሲያደርሱ ይችላሉ?**

**አቶ ደቻሳ፡-** ቁመት፣ ፆታ፣ ክብደት፣ አለባበስ፣... የራሱ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ በቁመታቸው አጭር የሆኑ አትሌቶች በውድድር ወቅት ረጅም አትሌቶችን ተጠግተው ቢሮጡ እንደጥላ መከለልና ከነፋስ ማምለጥ ይችላሉ። በተለይ የአየር እጥረት ያለበትና ከፍተኛ ሙቀት ያለበት አካባቢዎች ላይ ይህንን መሰል ቴክኒክ በመከተል ተጠቃሚ መሆን ይቻላል። ከፆታ አንጻርም ሴቶች በተፈጥሮ ሞቃታማ አካባቢዎች ይመቻቸዋል፤ ወንዶች ደግሞ በተቃራኒው። ዝግጅት በሚደረግበት ወቅትም እንደ ሱሉልታ ያሉ ቀዝቃዛ ስፍራዎች ለወንድ አትሌቶች በይበልጥ ተስማሚ ናቸው። ክብደትም ለመወርወርና አየር ላይ ለመንሳፈፍ የሚያግዝ በመሆኑ እንደየርቀቱ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። በአለባበስም ወንዶች ጥብቅ ያሉ ትጥቆችን አለመጠቀም ተገቢ ነው፤ ሴቶች ደግሞ ሙቀት ለሆነበት አካባቢ ነፋስን ሊያመጣ በሚችል መልኩ የፀጉር አሠራርን ማስተካከል። ይህ ሁኔታ ብቃትን የሚፈታተን መሆኑ ታውቆ ከምቹነቱ አንጻር ዝግጅቱንና ውድድሩን መወሰን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ቀደም በጋዜጣ ባሰፈሩት ጽሑፍ ላይ የቡድን ሥራን ከአዕዋፋት መማር እንደሚገባ አስቀምጠዋል። ይህን እንዴት ያብራሩታል?**

**አቶ ደቻሳ፡-** መረዳት ያለብን ነገር በምሕንድስና የላቀ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው የንብን ያህል ዲዛይን መሥራት እንደማይችል ነው። ወፎች ደግሞ በቡድን ሥራ የታደሉ ናቸው። አስቀድመው የአየር ሁኔታውን በመገንዘብ አንድን መስመር ተከትለው ያለኮምፓስ ረጅም ርቀት የሚጓዙ ሲሆን፤ በሌላ ጊዜም በዚሁ ሁኔታ ወደነበሩበት ይመለሳሉ። ቡድኑን የሚመራው ወፍ አየሩን እየሰነጠቀ (እየቀደደ) ሲበር ሌሎቹም ይህንኑ የተመቻቸ መንገድ ተከትለው ይጓዛሉ። የመሪነቱ ስፍራ አድካሚ በመሆኑም ከቆይታ በኋላ በሌላኛው ተተክቶ አቅም ያበጃል። በዚህ ሁኔታም እየተቀያየሩ ሃገር ማቋረጥ ይችላሉ። አትሌቶችም ይህንኑ አካሄድ መከተል ይገባቸዋል፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ቀድመው በመሮጥ ስለሚታወቁ ተፎካካሪዎቻቸው እነሱን ከለላ ማድረግን ተለማምደዋል። ይህንን አካሄድ ለመተግበርም አቅማቸውን፣ የአየሩን ሁኔታና የሩጫውን ስሜት መለየትና ስልትን መቀያየር ያስፈልጋል። ተፎካካሪዎቻችን የኢትዮጵያውያን አትሌቶችንን ቀዳሚነት ተገን አድርገው በመሮጥና ትንፋሽ በመያዝ በመጨረሻው ሰዓት ወደፊት በመምጣት እየቀደሟቸው ይገኛል።

> **ከዚህ ቀደም በከፈልኩት መስዋዕትነት አልቆምም አሁንም ቢሆን በሙያዬ ለማገልገል ዝግጁ ነኝ፣ ይህንን የማደርገውም ለገንዘብ ብዬ ሳይሆን የዜግነቴን አስተዋፅዖ ለማበርከት ነው**


ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

**አዲስ ዘመን፡- ከስፖርቱ ጋር በተያያዘ የሠራቸውን መሰል ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ተመልክተው ሲጠቀሙበት ጥረት አድርገው ያውቃሉ?**

**አቶ ደቻሳ፡-** በተለያየ መንገድ በተለያዩ ጊዜያት የብሔራዊ ቡድን አሠልጣኞችን አፈላልጌ ለማስረዳት ሞክሬያለሁ። ነገር ግን ከአብዛኛዎቹ ጋር መግባባት አልቻልንም። ለዚህ እንደማሳያ የሚሆን አንድ ክስተት ማስታወስ እንችላለን፤ ሞምባሳ በተካሄደው የዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና በተመሳሳይ አካባቢ ተወልደው ያደጉና በስኬታማነት ደረጃ ላይ የሚገኙ አትሌቶች ተሳትፈው ነበር። በወቅቱ ቡድኑ ወደ ውድድሩ ከመጓዙ አስቀድሜ ልምምድ የሚሠሩበት ጃንሜዳ ድረስ በመሄድ ሁኔታውን ለመግለጽ ሞክሬ ነበር። ቅዝቃዜ የለመዱ አትሌቶችን በከፍተኛ መጠን ሞቃት ወደሆነ አካባቢ መውሰድ ከፍተኛ ጉዳት ላይ ሊጥላቸው እንደሚችል ብናገርም ሰሚ ባለማግኘቴ እነቀነኒሳ በቀለን የመሳሰሉ ምርጥ ሯጮች መቋቋም አቅቷቸው ለማቋረጥ ተገደዱ። ይህ አቅምን መግደል ማለት ነው።

በ2008ቱ የቤጂንግ ኦሊምፒክም በተመሳሳይ ምክረ ሃሳብ ለአትሌቶች ሰጥቼ ነበር፤ ነገር ግን ሊሰሙኝ ስላልፈለጉ ማግኘት ከነበረብን ሜዳሊያ ያነሰ ነበር ያገኘነው። ከዚህ ባሻገር በተለያዩ ጋዜጣዎች ላይ ከሙያዬ አንጻር እንደ አንድ ሃገር ወዳድ ባለሙያ በተከታታይ በመጻፍ ግንዛቤ ከመፍጠር ወደኋላ አላልኩም። ከዚህ ቀደም በከፈልኩት መስዋዕትነት አልቆምም አሁንም ቢሆን በሙያዬ ለማገልገል ዝግጁ ነኝ፣ ይህንን የማደርገውም ለገንዘብ ብዬ ሳይሆን የዜግነቴን አስተዋፅዖ ለማበርከት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም ማንሳት የሚፈልጉት ሃሳብ ካለ?**

**አቶ ደቻሳ፡-** የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ቀናነትን ተላብሰን መሥራት ብንችል ለሁሉም የሚበጅና የሚረዳ ሥራ ማከናወን እንችላለን። በስፖርቱም ሆነ በሌላውም **ዘርፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስም እንችላለን።**

**አዲስ ዘመን፡-** አቶ ደቻሳ ለሰጡን ጊዜና ሙያዊ አስተያየቶች ከልብ እናመሰግናለን።